# ምዕራፍ ፵

# ከሃምሳ ዓመታት በኋላ ከሙሉ ጊዜ አገልግሎት መሰናበት

## 50 ዓመት በወንጌል አገልግሎት

*በ1995 ዓ.ም ኬዳሞ አሜሪካን ምድር ሲያገለግሉ ቆይተው ወደ አገራቸው ተመለሱ። እዚያ ሳሉም 50ኛ ዓመት የአገልግሎት ክብረ በዓላቸው ተከብሮላቸው በደስታ ነበር የተመለሱት።*

*በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽ/ቤትም ለ50 ዓመታት ቤተ ክርስቲያኒቱን ሲያገለግሉ መቆየታቸውን በማሰብ የ50ኛ ዓመት በዓል ተዘጋጀ። ወንጌላዊው በቃለ ሕይወት በኩል ሆነው ዞረው ላገለገሏቸው በረከት የሆኑአቸው ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በሙሉም በዓሉን እንዲታደሙ ጥሪ ተላለፈ።*

*በዓሉም ወንጌላዊው እንደገና ለአገልግሎት የሚነሳሱበትና ስላበረከቱት አገልግሎት የሚባረኩበት ትልቅ መነቃቂያ ሆኖ ተከበረ። ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት፣ የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን፣ ገነት ቤተ ክርስቲያን… ሌሎችም ብዙዎች በበዓሉ ላይ ተገኝተው ስላበረከቱት የ50 ዓመታት አገልግሎት ወንጌላዊውን ባረኩ።*

*አንዳንዶች ወርቅ፣ ሌሎች ብር፣ ሌሎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ እና ሌሎች መጻሕፍት፣ አንዳንዶችም አልባሳትና ሌሎችም በርካታ ስጦታዎችን ለወንጌላዊው በስጦታ አበረከቱላቸው። ብዙዎች እየተነሱም ስለ ወንጌላዊው በጽናት የሰጡአቸውን የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎቶች ምስክርነት ሰጡ።*

*በዚሁ ዕለት ወንጌላዊው አስቀድመው ሲያገለግሉ የነበሩትን የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ ወንጌላዊነት ለማቆም የወሰኑ ቢሆኑም በቀጣይ ዘመናቸው እግዚአብሔር በሚሰጣቸው እድሜ ሲሠሩ ያቀዱትን የአገልግሎት እቅድ በጽሑፍ አዘጋጅተው ለበዓሉ ታዳሚዎች አነበቡ። ከዚህ በኋላም እንደገና ለአገልግሎት*

*በመዘርጋት ጌታን በማገልገል እንደሚቀጥሉም ተናገሩ። ለአዲስ ምዕራፍ የወንጌል አገልግሎትም ተዘጋጅተው ተነሱ።*

*አስገራሚ አጋጣሚ ሆኖም የወንጌላዊው የ50 ዓመት የሕይወት ጉዞን የሚዳስስ ጽሑፍ በዚሁ የሕይወት ታሪክ ጸሑፍ አቀናባሪ ተሰናድቶ ለበዓሉ ታዳሚ በአንድ አባት ተነበበ። ጽሑፉ በቃለ ሕይወት መጽሔት ላይም ታተመ።*

---------------------//------------------

## ስንብት

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ጥሩ የአገልግሎት ቦታ ነበር። የወቅቱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያደረጉትን ሳስብም ጽሕፈት ቤቱን በጣም እንድወድደው ያደርገኛል። እኔ በ1994 ዓ.ም ወደ አሜሪካ ከመሄዴ በፊት ለመልቀቅ ወስኜ ደብዳቤ ባስገባም እነርሱ ወዲያውኑ እሺ ብለው ሊለቅቁኝ ስላልፈለጉ እስከ 1996 ዓ.ም ታህሳስ ወር ድረስ የዋና ጽሕፈት ቤቱ አገልጋይ ሆኜ ቆይቻለሁ። በመጀመሪያ ገና የመልቀቅ ሃሳቤን በጽሑፍ እንዳስገባሁ የወቅቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ጸሐፊዎች የነበሩት ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ፤ አቶ ኩርሴ ሸፈኖ እና አቶ ደስታ ደምሴ ሆነው ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ወስደው ዕራት ጋብዘው ምክንያቱን ጠይቀውኛል። በሆቴሉ 10ኛ ፎቅ ላይ ተቀምጠን ዕራት እየተመገብንም ብዙ ተወያይተናል። እኔም አስቀድሜ የተረክሁላችሁን ሁለት ምክንያቶች ተናግሬ ከዮሐንስ ጋር ስለነበረን ሙግት እና ስለደረስንበት ውሳኔ ሳልናገር በቀጥታ ዮሐንስ እኔን እንደሚተካኝ ብቻ ገለጽኩላቸው። በውስጤ የተፈጠረ ሌላ ቅሬታ ካለም እንድነግራቸው ፈልገው ነበር። ነገር ግን እኔ ምንም ቅሬታ እንደሌለኝ ተናግሬ ነገሩን ዘጋሁ።

ይህን መሰሉን ውይይት በመጨረሻም ልሰናበት ተስማምተን ከጨረስን በኋላም እንደገና አቶ ኩርሴ እና ዶ/ር ተስፋዬ ሐራምቤ ሆቴል ወስደው ጋብዘው አነጋግረውኝ አሁንም ተመሳሳይ መልስ ሰጥቻቸዋለሁ። በዚህ ጊዜ ዶ/ር ተስፋዬ ውሳኔዬን እንደሚቀበሉ ነገር ግን እኔ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለኝ ግንኙነት በደመወዝ እና በቋሚ ሠራተኛነት መሆኑ ቢቀርም በጀመርኩት አገልግሎት አማካኝነት አሁንም የቃለ ሕይወት አገልጋይ ሆኜ እንደምቀጥል ተናግሮ ተለያየን።

በእርግጥ እኔ የመልቀቅ ውሳኔ ላይ ከደረስኩ በኋላ ሃሳቤን እንድለውጥ የሚያስገድድ አንድ ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። ለመልቀቅ ወስኜ ደብዳቤ ካስገባሁ በኋላ ዋና ጽ/ቤቱ አንድ ውሳኔ ወስኖ ነበር። ይህ ውሳኔም ከዚህ ቀደም የኛ አገልግሎት ልክ እንደ አንድ መምሪያ በም/ዋና ጸሐፊ (የመንፈሳዊ ዘርፍ ኃላፊ) ቀጥታ ተጠሪነት ስር የነበረ ሲሆን ያንን የሚያስቀይር ነበር። እናም አገልግሎቱ ከዚህ ቀደም የተሰጠው ትኩረት ተቀንሶ በአንድ መምሪያ ስር እንደ አንድ ክፍል ተደርጎ ነበር።

ይህንን ነገር እንዳየሁም በቀጥታ ተቃወምኩ። እኔና ሌሎች የአገልግሎት ቡድን አጋሮቼ በጋራ ሆነን በዚሁ ጉዳይ ላይ ዶ/ር ተስፋዬ እና አቶ ኩርሴን አነጋገርን። እኔም በጣም ቅር ተሰኝቼ የተደረገውን አለመቀበላችንን ከነገርኳቸው በኋላ እንደውም የመልቀቅ ሃሳቤን ትቼ በዚሁ አገልግሎት እንደምቀጥል ተናገርኩ። ዶ/ር ተስፋዬም የአንድን ነገር አካሄድ የሚረዳ አስተዋይ የአስተዳደር ሰው ስለነበር ነገሩ እንደሚስተካከል ገልጾ ተስማምተን ተለያየንና ጥያቄአችን በመመለሱ የኔም መልቀቅ እውን ሆነ።

ዋና ጽሕፈት ቤቱ መሸኛ እስኪሰጠኝም ድረስ እኔ በደብዳቤ ባስታወስኩት መሠረት ከዕድሜዬ መግፋት ጋር በተያያዘ (በዓመት ለእኔ 82 ጣቢያዎች ላይ ተዟዙሮ ማገልገል በጣም አድካሚ እና ጎጂ ስለነበር) የአገልግሎት ስልት እንቀይር ብዬ ያቀረብኩት ሃሳብ ተቀባይነት አጥቶ እኔ ለማቆም ከወሰንኩበት ጊዜ ጀምሮ ከብሔራዊ ወንጌላውያን የቀድሞ አገልግሎት ተለየሁ። ከዚያም ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ የአገልግሎቱ መስክ የወንጌላውያን አገልግሎት ሆኖ ወንጌላውያንን ወደማሰልጠን እና እኔ ያዘጋጀኋቸውን የትምህርት መጻሕፍት የማስተማር አገልግሎት ጀመርኩ። ከዋና ጽሕፈት ቤቱ በ1996 ዓ.ም ታህሳስ 30 እስክሰናበት ድረስም ይህንን አገልገሎት ስሰጥ ቆየሁ።

ይህ አገልግሎቴ በዋነኛነት መሠረት ያደረገው "የወንጌል ዓላማ፣ ተልዕኮ እና አፈጻጸም" በሚል ርእስ ያዘጋጀሁትን መጽሐፍ ማስተማር ላይ ሲሆን በተለያዩ ቀጣናዎች፣ ኅብረቶች፣ ክፍለ ማኅበራት እና አጥቢያዎች ሳይቀር ለአገልጋዮች ስልጠና ይዘጋጅ እና አጥቢያዎች ሳይቀር ይሳተፉ ነበር። እኔም ለሦስት ቀናት ብቻዬን ሙሉ ሥልጠና ከሰጠሁ በኋላ ከዚያም አስተናጋጆቹ ቤተ ክርስቲያናት በሚያዘጋጁት ኮንፍረንስ ላይ አገልግዬ እመለሳለሁ።

ይህን አገልግሎት እንድሰጥ ከተመደብኩ በኂላም ከአንድ ዓመት በላይ በዋና ጽሕፈት ቤቱ በነበረኝ ቆይታ ለአገልግሎት ስወጣ መኪና እየተመደበልኝና ጥሩ ደመወዝ እየተከፈለኝ የቀድሞ ነገር ምንም ሳይጓደልብኝ ቆየሁ። በመጨረሻም ታኅሳስ 30 ቀን 1996 ዓ.ም ከዋና ጽሕፈት ቤቱ የሙሉ ጊዜ አገልጋይነት በክብር ተሰናብቼ ተሸኘሁ።

ከቃለ ሕይወት ወርሃዊ ደመወዝ ተከፋይ አገልጋይነት ስሰናበት ሥራውን ለማቆም የወሰንኩበት ከጥቅም ጋር የተያያዘ ምንም ነገር አልነበረም። እንደውም ያኔ ይከፈለኝ የነበረው 1,646.00 ብር በዚያ ወቅት የእኔን መሰል አገልግሎት ከሚሰጡ ሁሉ የተሻለ ነበር። ነገር ግን እኔ ሕይወቴንና ምስክርነቴን ለመጠበቅ እና አገልግሎቴ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ለመለየት ወሰንኩ። እግዚአብሔርም አገልግሎቴን እንደሚያስቀጥል የተስፋ ቃል ሰጥቶኝ ነበር።

የኔ ሥራ ማቆም እውን ሆኖ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ጽሕፈት ቤት ስለያይ ምንም እንኳን ከ50 ዓመታት በላይ ያገለገልኳት ቤተ ክርስቲያን ዲላ ብሄድ ለቃለ ሕይወት፣

ማረቆ ብሄድ ለቃለ ሕይወት፣ ሻሾን ብቆይ ለቃለ ሕይወት፣ በቢቾ ከኤስ. አይ. ኤም ጋር ሥራም ለቃለ ሕይወት፣ ጌጃ ቃለ ሕይወትም ስመጣ በአንዷቱ ቃለ ሕይወት ውስጥ የኖርኩ ቢሆንም ጽሕፈት ቤቱ የአገልግሎት ክፍያ ያዘጋጀልኝ የዋና ጽሕፈት ቤቱን የአገልግሎት ዘመኔን ቆጥሮ በማስላት ብቻ ነበር። ስለሆነም የሰባት ዓመታት አገልግሎቴ ተሰልቶ አስራ አንድ ሺ ብር እንድወስድ ተነገረኝ።

እኔም በዚሁ ነገር ላይ አሰብኩበት እና ገንዘቡ አይበቃም ብዬ ብሟገት ከዋና ጽሕፈት ቤቱ ወዴት ሄጄ እከስሳለሁ? በዚያ ላይ ገንዘብ አነሰ ብል ከቃለ ሕይወት ጋር የነበረኝ አንድነት እና ፍቅር ሊበላሽ ይችላል። የእኔ ምስክርነት እና የእግዚአብሔር መገልገያነቴም ይበላሻል በማለት ያለ ምንም ቅሬታ ለመወሰድ ተነሳሁ። ገንዘቡን ፊርሜ እንድወስድ ስጠየቅም ግጥም አድርጌ ፊርሜ የአገልግሎት ክፍያዬን ወሰድኩ።

እንዲሁ የአገልግሎት ክፍያ ሳይፈጽሙ የሸኙኝና ለገንዘብ አልሟገትም ብዬ የተውኳቸው ለሰባት ዓመታት ያገለገልኳቸው ኤስ. አይ.ኤሞች እና ለ22 ዓመት ያገለገልኳት ጌጃ ቃለ ሕይወትም ከቃለ ሕይወት ዋና ጽሕፈት ቤት በምሰናበትበት ጊዜ እግዚአብሔር አሳስቧቸው ሁለቱም አምስት፣ አምስት ሺህ ብር ሰጥተውኛል።

# ምዕራፍ ፶፩

# ነጻ አገልግሎት

## ሳማሪታን ፐርስ እንደገና መጣ

*ወንጌላዊ ኬዳሞ ከኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ተሰናብተው በራሳቸው እቅድ እና ፕሮግራም በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወሩ ማገልገል ቀጥለዋል። እግዚአብሔር አስቀድሞ በሰጣቸው ተስፋ መሠረትም እኚህ አንጋፋ አባት የእድሜ መግፋት ሳይገድባቸው አሁንም በመላ አገሪቱ እየተዘረጉ አገልጋዮችን የማሠልጠን ሥራቸውን ተያይዘውታል።*

*በዚሁ ወቅት የእርሳቸው ጥንካሬ እና ለአገልግሎት የመዘርጋት ፈቃደኝነትም እንዳለ ቢሆንም ሁል ጊዜ ለአገልግሎት በተንቀሳቀሱ ቁጥር የሚገጥማቸው አንድ ፈተና ከፊታቸው ተጋረጠ።*

*ይህንኑ አገልግሎት ለማስቀጠል ወንጌላዊው ሙሉ ፍላጎት ስለነበራቸውም ለጉዞ የሚኖራቸውን ወጪ መሸፈን አዳጋች የሚሆን ከሆነ ከቃለ ሕይወት፣ ከኤስ. አይ. ኤም እና ከጌጃ የተቀበሉትን የዓመታት የአገልግሎት ማካካሻ ገንዘብ ለመጠቀም አቅደዋል። ይሁንና ወንጌላዊው ለጉዞ በተነሱ ቁጥር ለትራንስፖርት መገልገያ የሚሆን መኪና ከዋና ጽሕፈት ቤቱ መጠየቅ ወይም ደግሞ በሕዝብ ትራንስፖርት መጠቀም ነበረባቸው። የሕዝብ ትራንስፖርት በመጠቀም በተለይ ወደ ገጠራማ የአገሪቱ ክፍሎች መጓዝ ደግሞ ለኬዳሞ ዓይነት 75 የሚያህሉ ዓመታትን በዕድሜ ላስቆጠረ አዛውንት ከባድ ነው። ስለሆነም ወንጌላዊው ወደ ዋና ጽሕፈት ቤቱ ሄደው መኪና በመለመን ሲታጣም ከአገልግሎት በመቅረት አጣብቂኝ ውስጥ ገቡ።*

*በዚሁ መልክ የተጀመረው አገልግሎት የመቆም ስጋት ሲጋረጥበት የኬዳሞ አምላክም በዚያው ዓመት መልሱን ይዞ መጣ።*

*ኬዳሞ ከዋና ጽሕፈት ቤቱ በተሰናበቱበት 1996 ዓ.ም ውስጥ አንድ ወቅት ላይ ወደ ሲዳማ አለታ ወንዶ ሄደው አገለገሉ። በዚሁ ለአገልግሎት በሄዱበት ቦታም 123 ያህል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ተሰባስበው በወንጌላዊው አስተማሪነት በመማር ላይ ነበሩ። ኬዳሞ በተለመደው ትጋት እና በአገልግሎት ፍቅር አንዴ ሞቅ አንዴ ቀዝቀዝ በሚል*

ስሜት በክፍሉ የሞሉትን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አትኩሮት ወደ የእግዚአብሔር ሃሳብ ለማስጠጋት ይጥራሉ። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም በአገልጋዮቹ ልብ ላይ የተሃድሶ እና ለወንጌል የመነሳት ቅናትን እየፈጠረ ያቀጣጥላቸዋል።

ይህ እየተካሄደ በነበረበት ሰዓትም በድንገት ከየት መጡ የማይባሉ የውጪ አገር ዜጎች (ፈረንጆች) በአለታ ወንዶ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ ተገኙ። አብረዋቸው ከነበሩት የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ቤት ጽሕፈት ሠራተኞች ጋር በመሆንም የቤተ ክርስቲያኒቱን ቅጥር ግቢ ይጎበኙ ጀመር።

በድንገትም ኬዳሞ እያስተማሩ ወደ ነበረበት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ክፍል ገቡ።

ከእነዚሁ ሰዎች መካከልም የሳማሪታንስ ፐርስ ዳይሬክተር የሆነው ኬን አይዛክ የተባለ ሰው ነበረበት። ኬን አይዛክ ከሃያ ዓመታት በፊት የወቅቱ የሳማሪታንስ ፐርስ ዳይሬክተር ከነበረው ከፍራንክሊን ግራሀም ጋር ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረ እና ከዚያም በኋላ ሳማሪታንስ ፐርስ ከቃለ ሕይወት ጋር በምትሠራቸው የልማት ሥራዎች ሰበብ በተደጋጋሚ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ ሰው ነበር። ሳማሪታንስ ፐርስ ከ20 ዓመታት በፊት ኬዳሞ በአዲስ አበባ የሚንቀሳቀሱበት መኪና እንደሌላቸው ለፍራንክሊን ግራሃም ነግረው ቮልስ ዋገን የገዛላቸው ተቋም እንደሆነ ያስታውሷል።

ኬዳሞ በማስተማር ላይ እያሉ የገቡት እነዚሁ ሰዎችም ይቅርታ ጠይቀው በአዳራሹ ውስጥ የሚደረገውን ነገር ማየት ጀመሩ። ኬን አይዛክስም በጊዜው በማስተማር ላይ የነበሩትን ወንጌላዊ ተመልክቶም ዝም ማለት አልቻለም። "አንተ ሰው አሁንም እያገለገልክ ነው?" ብሎ በመገረም ጠየቀ፡ ህንጌላዊውም እዚያው በተማሪዎቻቸው ፊት ጮክ ብለው "አዎ አሁንም እያገለገልኩ ነው፤ አሁን ደመወዝ የለኝም፤ ጡረታም የለኝም፤ የምንቀሳቀስበት መኪናም የለኝም፤ ነገር ግን አገለግላለሁ።" አሉ። ሳማሪታንስ ፐርስን የወከለው ፈረንጅም ለመኪና እንጸልያለን ብሎ መለሰ።

እግዚአብሔር የተናገረውን ለመፈጸም የሚተጋ ታማኝ አምላክ ነው እና ኬዳሞ በመላ አገሪቱ እየዞሩ ማገልገላቸውን እንደሚቀጥሉ የሰጣቸው ተስፋ እንዳይቆም ሳማሪታንስ ፐርሶችን እንደገና ሊጠቀም ይህንን አጋጣሚ ፈጠረ። የሳማሪታንስ ፐርስ ኃላፊዎች ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ የቃለ ሕይወት ዋና ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎችን ሃሳብ ጠየቁ። እነርሱም በነገሩ ላይ መልካም ፈቃዳቸውን ገለጹ። ወዲያውኑም ለወንጌላዊው የመስክ አገልግሎት የሚስማማ ሚትስቡሺ ባለሁለት ጋቢና መኪና ተገዛ። ወንጌላዊ ኬዳሞም ያለ ስጋት ወደ መላ ኢትዮጵያ ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅና ምዕራብ ዳርቻዎች መዘርጋታቸውን ቀጠሉ።

............................//............................

## እንደገና ወደ መላው ኢትዮጵያ መዘርጋት

አዎ! እግዚአብሔር ታማኝ አምላክ ነው። በኔ ሕይወት መሥራት የጀመረውን ሊጨርሰው ወዷል እና እንደገና የሚያስፈልገኝን እየሰጠ በመላ አገሪቱ ያዞረኝ ጀመር። የሳማሪታንስ ፐርስ ሰዎች በአለታ ወንዶ ካገኙኝ በኋላ ወዲያውኑ ለዋና ጽሕፈት ቤቱ መኪና ሊገዙልኝ ጥያቄ አቀረቡ። እነ ዶ/ር ተስፋዬም ስምምነታቸውን ገለጹ። በጊዜው ምክትል ዋና ጸሐፊ እና የልማት ዘርፍ ኃላፊ የነበረው ወንድም ደስታ ደምሴም ከፈረንጆቹ ጋር አለታ ወንዶ አግኝቶኝ ነበር። ከዚያም በኋላ ለኔ የገጠር አገልግሎት የሚሆነውን መኪና በመምረጥ ረዳኝ። እኔ ገና መኪናውን የሚገዛ ረጂ ሳይገኝ በፊት በነበረን መሻት አነስ ያለ ለገጠርም ለከተማም የሚሆን ሱዙኪ ቪታራ ቢኖረኝ ብዬ አስብ ነበር። ሳማሪታንስ ፐርሶችም ለመኪናው መግዣ የሚሆን 340 ሺህ ብር ላኩ።

መኪናውን እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ ለመግዛት ስንንቀሳቀስ ግን ገጠር መንገድ ሊያገለግል የሚችል ጠንካራ መኪና መሆን እንዳለበት በማሰብ ሚቲስቡሺ ፒክ አፕ ለመግዛት ወሰንን። ዋጋው ከፍ ይል ስለነበርም እኔ ከራሴ 30,000 ብር ጨምሬ ጠንካራ መኪና ገዛንና ላለፉት አስር ዓመታት ለነበረኝ አገልግሎት ጠንካራ መገልገያ አገኘሁ።

በእነዚህ ዘመናት የነበረኝ አገልግሎት በአብዛኛው አስቀድሜ በዋና ጽሕፈት ቤቱ የመጨረሻ ቆይታዬ የጀመርኩትን "የወንጌል ተልዕኮ እና አፈጻጸም" መጽሐፍ ማሰልጠን ነበር የቀጠልኩት። ለዚህ ሥልጠና እንስተኛ መጽሐፍ አዘጋጅቼ ለሰልጣኞች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲሸጥ ታተመ። አስር ሺህ ኮፒ መጻሕፍትም ለሠልጣኞች ብቻ በኔ በራሴ አማካኝነት እየተሸጠ ገንዘቡ መጽሐፉን ላሳተመው ለዋና ጽሕፈት ቤቱ መንፈሳዊ ዘርፍ ገቢ እየተደረገ ተሰራጨ። በብዙ ቦታዎች እየተዟዟርኩም በተለያየ ዓላማ የወንጌል አገልጋይ ሆነው ለተሰማሩ የቤተ ክርስቲያኒቱ ወንጌላውያን እና አገልጋዮች በወንጌል ተልዕኮ ላይ እንዲያተኩሩ እና እንዴት ባለ መልኩ ተልዕኮአቸውን መፈጸም እንዳለባቸው ሳስተምር ቆየሁ።

ይህን መጽሐፍ ካጠናቀቅሁ በኋላም ሌላ የሥልጠና መጽሐፍ አዘጋጀሁ። እናም ይህንን "ክርስቶስን መሰል ሕይወት እና አገልግሎት" የሚል መጽሐፍ አሁንም በአነስተኛ ይዘት አዘጋጅቼ በዋና ጽሕፈት ቤቱ አማካኝነት እየታተመ በየሥልጠናው ቦታ እያሰራጨሁ ሳገለግል ቆየሁ። ይህንን መጽሐፍ እኔ ብቻ ከሥልጠና በኋላ ለሠልጣኞች እየሸጥኩ የአሥር ሺህ ኮፒ ገንዘብ በዋና ጽ/ቤቱ አማካኝነት ተመላሽ ማድረግ ችያለሁ። ትምህርቱም ሥልጠናውን በወሰዱ አገልጋዮች ሁሉ ዘንድ በጣም ተወዳጅ ነበር።

በዚህ ትምህርት ውስጥ አስር መሰረታዊ ነጥቦች የነበሩ ሲሆን እነርሱም የሚከተሉት ነበሩ፡-

1ኛ የክርስቶስ ማንነት እና አገልግሎት፤

2ኛ ክርስቶስ ለእኛ መስዋዕት እንደሆነ እኛም ራሳችንን ለእርሱ መስዋዕት ማድረግ፤

3ኛ የክርስቶስን ዓላማ፣ ተልዕኮ እና ባህርይ ይዞ ወደ አገልግሎት መግባት፤

4ኛ በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መካከል ጤናማ፤ እርስ በእርስ የመተጋገዝ የመደጋገፍ ግንኙነት መፍጠር፤

5ኛ የቤተ ክርስቲያን አባላትን በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት በቁጥር እና በመንፈሳዊ ሕይወት ብስለት ማሳደግ፤

6ኛ አገልጋይ፣ ጥሪው፣ ጠሪው እና የጠሪው ዓላማ፤

7ኛ ወደ ሥራ ለመሰማራት መደረግ ያለባቸውን ነገሮች ማወቅ፤

8ኛ ሁል ጊዜ በእርሱ ታምኖ መሄድ፦

9ኛ በሁሉ ነገር የማያሳፍር፤ በቅንነት የሚናገር፤ በቃሉ እና በመንፈሱ የሚመራ ሠራተኛ መሆን፣

10ኛ ሁል ጊዜ ኢየሱስን መስማት (አብ እርሱን ስሙት እንዳለ) የሚሉት ነበሩ።

እግዚአብሔር እንደተናገረኝም ከዋና ጽሕፈት ቤቱ ከለቀቅሁ በኋላ በበርካታ የአገሪቱ ክፍሎች እየተዘዋወርኩ ማገልገል ጀመርኩ። ጎፋ (ሳውላ)፣ አርባ ምንጭ፣ ከምባታ ውስጥ ሺንሺቾ እና ዶዮገና ቦቢቾ እና ሻሸጎ ... በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች በተደጋጋሚ እየተጠራሁ አገልጋዮችን በማሰልጠንና በኮንፍራንሶች ላይ በመስበክ የወንጌል ቃል ኪዳኔን ጠብቄ ማገልገሌንም ቀጠልኩ። በብዙ ቦታዎች ስለ ጤናማ ግንኙነት የሚናገረውን ምዕራፍ ሳስተምር እርስ በእርስ የተጋጩ አገልጋዮች እኔ እያስተማርኩ ባለሁበት ክፍል ውስጥ በእምባ እየተራጩ ይታረቁ ነበር። እኔ በሄድኩበት ቦታ ሁሉ በትምህርቱ ማብቂያ ላይ ጌታ ኢየሱስ ሐዋርያቱን አንበርክኮ እንደዳሰሳቸው ሁሉ ጉባኤው በሙሉ በጌታ ፊት ቃል ኪዳን እየገባ ተንበርክኮ ይጸልይ ነበር። በዚህም በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች እና በየቤተ ክርስቲያኑ የሚያገለግሉ አገልጋዮች በንስኃ በጌታ ፊት አልቅሰዋል። ጨንቻ፣ ወላይታ (ሶዶ)፣ ዲላ፣ ይርጋ ጨፌ፣ ... መንፈስ ቅዱስ አስደናቂ የተሐድሶ ጊዜን ለቤተ ክርስቲያን ሲሰጥ የዓይን ምስክር ነበርኩ።

ሠልጣኞቹ ከሥልጠናው በኋላ ያዘጋጀሁትን መጽሐፍ በቅናሽ ዋጋ ገዝተው እየወሰዱ ለአገልግሎታቸው ይጠቀሙበታል። ያኔ የመንፈሳዊ ዘርፍ ኃላፊ ከነበሩት (ምክትል ዋና ጸሐፊው) ከአቶ ኩርሴ ሽፈዮ ጋር ተመካክረን ለመጻሕፍቱ የተመነነው ዋጋ

በጣም አነስተኛ ስለነበርም ያለ ችግር በደስታ ገዝተው በመወሰድ ይጠቀሙባቸው ነበር።

እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ጠባቂ ታማኝ አምላክ ስለሆነ ከኔ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ጠብቆ በቃለ ሕይወት አማካኝነት ሳገለግለው እንደነበረው ለብዙ ቤተ ክርስቲያናት በብዙ ቦታ እንዳገለግለው እንደገና የሚያስፈልገውን ሁሉ አመቻችቶልኝ ነበር። ሁለቱን መጻሕፍት ሁለት ሁለት ጊዜ አሳትሜ ሥልጠና ስሰጥ ከቆየሁ በኋላም እንደገና ወደ ሌላ ምዕራፍ ተሸጋገርኩ። የ1ኛ ጢሞቴዎስ ማስተማሪያ አነስተኛ መጽሐፍ (አስቀድሜ ያዘጋጀሁት) እንዲታተም ተደርጎ በእርሱ ላይ ሥልጠና መስጠት ጀመርኩ።

በዚያ ዘመን የነበረው አገልግሎቴ በእርግጥ ይህ ብቻም አልነበረም። እግዚአብሔር በጌጃ ቃለ ሕይወት ስሰጥ በነበረው አገልግሎት አማካኝነት በመላው አዲስ አበባ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት እንድታወቅ እና እንዳገለግል በር ከፍቶልኝ ነበር። በዚህ መሰረትም በዓመት ውስጥ ለበርካታ ሰንበቶች በልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት እየተዘዋወርኩ አገለግል ነበር። በሙሉ ወንጌል፣ በመሠረተ ክርስቶስ፣ በገነት እና በአዳዲሶቹ እንደነ አማኑኤል ኅብረት ባሉ ቤተ ክርስቲያናት ሳይቀር እየተጠራሁ በብዙ ቦታዎች ወንጌል ሰብኬያለሁ፤ እግዚአብሔርም እንደገና ለብዙ ሕዝብ እና ወገን በረከት አደረገኝ።

ይህንን ሁሉ አገልግሎት እንድሰጥም እግዚአብሔር አስቀድሞ እንዴት ባለ ስልት መመራት እንዳለብኝ አስተምሮኝ ነበር። ከዋና ጽሕፈት ቤት ለመልቀቅ ከወሰንኩባቸው ምክንያቶች አንዱ የዕድሜዬ ጉዳይና የጤናዬ ሁኔታ ነበር። እንደኔ ላለ ሰባት አስርት ዓመታትን ላስቆጠረ ሰው እረፍት የግድ አስፈላጊ ነበር። ድሮ እኔ ያለ ዕረፍት የአገልግሎት በር በተከፈተበት ሁሉ እሮጥ የነበረ ሲሆን አሁን ግን አገልግሎት የምቀበለው በተጨናነቀ ሁኔታ አልነበረም። በእርግጥ እግዚአብሔር ይህንን ያስተማረኝ ቀደም ብሎ ነበር።

በ1989 ዓ.ም ወደ እስካንዴኒቪያን አገሮች ሄጄ ባገለገልኩበት ወቅት አንዲት አማኝ የሆነች ኢትዮጵያዊት ነርስ አግኝታኝ ነበር። ይህቺ እህት የጤናዬን፣ የእድሜዬን ሁኔታ እና የአገልግሎት ውጥረቱን አይታ አንድ ምክር መክራኝ ነበር። አገልግሎቱን ከእድሜዬ ጋር አመጣጥኜ ጥሩ እረፍት እያገኘሁ ካላገለገልኩ በዚሁ ትጋቴ መቀጠል እንደማልችል አስጠነቀቀችኝ። ይሁንና እኔ ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለስኩ ምክሯን ተግባራዊ አላደረግሁም ነበር። ይልቁንም ከ1991 እስከ 1994 ዓ.ም ማብቂያ ድረስ እረፍት አልባ በሆነ የጉዞና የአገልግሎት ፕሮግራም መላ አገሪቱን ያለ ዕረፍት ስናዳርስ ቆየን።

በመጨረሻ ግን እኔ የራሴን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በቂ ዕረፍት እየወሰድኩ ለማገልገል ወሰንኩ። በዚህም መሠረት ከዋና ጽሕፈት ቤቱ ከለቀቅሁ በኋላ በየዓመቱ የራሴን የአገልግሎት ፕሮግራም ማውጣት ጀመርኩ። የዓመት እቅዴንም አቅዳለሁ።

በዕቅዴ መሠረትም በዓመት ውስጥ በሚመጣልኝ የአገልግሎት ጥሪ መሠረት ሳይሆን አስቀድሜ በስንት ቦታዎች ኮንፍረንስ ላይ እንደማገለግል፣ ስንት ቦታ ሥልጠና እንደምሰጥ፣ ስንት ቦታ በሚደረግልኝ ጥሪ የእሁድ አምልኮ ላይ ተገኝቼ እንደምሰብክ እወስናለሁ።

በእቅዴ ውስጥ በዓመት ለ12 ጊዜያት ብቻ የሥልጠና ጊዜ መድቤ እይዛለሁ። ከከተማ እና ከገጠር አብያተ ክርስቲያናት ለሚደረግልኝ የስብከት ጥሪ በወር ሁለት ጊዜ እና በተለየ ሁኔታ በሚዘጋጁ ኮንፍረንሶች ላይ በዓመት ውስጥ ለ6 ጊዜያት ያህል ብቻ ለማገልገል እቅዱን እነድፋለሁ። በዚህ መሠረት የሚደረጉልኝን የአገልግሎት ጥሪዎች አቀናጅቼ አገለግላለሁ። ይኸው አገልግሎቴም በእግዚአብሔር ኃይል እስከ አሁን ድረስ መቀጠል ችሏል።

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም እንደ አንድ አማካሪ አባትና፣ የወንጌል ባለ አደራ በመቁጠር ችግር ሲፈጠር፣ ልዩ ፕሮግራም ሲኖር የፕሮግራሙ ተካፋይ እንድሆን፣ ቃሉን እንድሰብክ እና አባታዊ ጸሎት እንዳደርግ ሁል ጊዜ ጥሪ ታደርግልኛለች። በተለያዩ የቤተ ክርስቲያኒቱ ታላላቅ በዓላትም ሆነ ስብሰባዎች ላይ በክብር እንግድነት እገኛለሁ።

በዚህ መልኩ የሕይወት ጉዞዬ እየቀጠለ እያለም ቃለ ሕይወት በአንድ መርኃ ግብር ላይ እንድታደም ጥሪ አቀረበችልኝ። 46ኛው የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ በትግራይ ክልል ዋና ከተማ በመቀሌ ተዘጋጀ። እኔም ይህንኑ ጉባኤ እንድሳተፍ ጥሪ ተደርጎልኝ ለመሄድ ተዘጋጅቼ እያለሁ በድንገት አስደንጋጭ ነገር በኔ ቤት ተፈጠረ።

…………………//………………

# ምዕራፍ ፶፪

# የታደለች ሞትና የኔ እንደ ንስር መታደስ

## ወ/ሮ ታደለችም ተሞሽሩ (2000 ዓ.ም)

*ወንጌላዊ ኬዳሞ 50ኛ ዓመት የወንጌል አገልግሎት የወርቅ ኢዮቤልዩ በዓላቸውን አክብረው ከቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ደመወዝ ተከፋይ አገልጋይነት ተሰናብተዋል፡፡ ከዚህ በኋላም አሁን ያርፋሉ ቢባልም ወንጌላዊው ግን እንደ ቀድሞው በላቀ ትጋት በመላ አገሪቱ እየዞሩ ማገልገላቸውን ቀጥለዋል፡፡*

*በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት እና በሌሎች ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት እየተዘዋወሩም በዓመት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜአቸውን በመስበክ እና በማስተማር ያሳልፋሉ፡፡*

*በዚህ ሁኔታ እየኖሩ እያለም ታምመው ቤት የዋሉት የወይዘሮ ታደለች ጤና ወይ ሳይሻሻል አሊያም ከፍተኛ ወደ አስጊ ደረጃ ሳይሸጋገር አስር ዓመታትን ደፈኑ፡፡ በ2000 ዓ.ም አንድ ማለዳም ኬዳሞ እንደ ልማዳቸው ወፍ ሳይንጫጫ ተነሱ፡፡ በዚህ ዕለት ለአገልግሎት ወደ ቡታጅራ ይሄዱ ስለነበርም ከወትሮው አነሳሳቸው በተለየ መልኩ ለማለዳ ጉዞ የሚደረግ ዝግጅት ያለበትም ነበር፡፡ ወንጌላዊው ሁል ጊዜ ጠዋት ሲነሱ እንደሚያደርጉትም አጠገባቸው ጋደም ብለው ወደ ነበሩት ባለቤታቸው ዞረው አዳራቸውን ጠየቁ፡፡ "እንዴት አደርሽ?" አሉ ኬዳሞ፡፡ ወ/ሮ ታደለችም በስቃይ ስሜት "ዛሬ ከወገቤ በታች እያቃጠለኝ ነው፤ ኡ...ፍፍ... ተቃጠልኩ፡፡" ብለው መለሱላቸው፡፡*

*ወንጌላዊው ይኼኔ ከአልጋ ወርደው የተለመደ ተንበርክኮ መጸለያ ስፍራቸው ወደ ሆነው ሳሎናቸው ገቡ፡፡ በዚህ ጊዜ "መንግስተ ሰማያት እያለ እርሷ ለምን እዚህ ትሰቃያለች?" የሚል ጥያቄ በአዕምሮአቸው ውስጥ ይብላላ ጀመር፡፡ እናም በከፍተኛ ስሜት ከወ/ሮ ታደለች ሁኔታ ጋር በተያያዘ "እግዚአብሔር ሆይ ያንተ ፈቃድ ይሁን!" እያሉ ጸለዩ፡፡ "ለመሆኑ ያንተ ፈቃድ ምንድን ነው?" የሚል ጥያቄም አስከተሉ፡፡ ጸሎታቸውንም ጨርሰውም ለአገልግሎት ወደ ቡታጅራ አቀኑ፡፡*

*አርብ ምሽቱን እና ቅዳሜ ሙሉ ቀን አስተምረው ቡታጅራ አደሩ፡፡ እሁድ ቀን ግን ወደ ሌላ ቦታ ሄደው ሊያገለግሉ ሲነሱ ኃይለኛ ዝናብ ዘንቦ መንገድ ስለተዘጋ እዚያው*

ቡታጅራ በመቆየት በከተማው ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የእሁድ ማለዳ አምልኮ ፕሮግራም ላይ አገልግለው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። ሰባት ሰዓት አናቱ ላይም ቤት ደርሰው ምሳቸውን ከባለቤታቸው ጋር ተመገቡ። ከዚያም ቡታጅራ ስለሚቆዩ ሊቀሩ የነበረውን አንድ ሠርግ ለመታደም ከምሳ በኋላ ተነስተው ሄደው ላፍቶ አካባቢ የነበረው ሠርግ ቤት ተገኙ።

በዚያ እሁድ ዕለት ማታም በመደበኛው የቤተሰብ ጸሎት ፕሮግራማቸው መሠረት ወንጌላዊ ኬዳሞ ከወ/ሮ ታደለች ጋር አብረው ጸለዩ። በዚሁ ጊዜ ኬዳሞ አርብ ዕለት የጀመሩትን ጸሎት ቀጥለው "የአንተ ፈቃድ ይሁን" እያሉ እግዚአብሔር በወ/ሮ ታደለች ሕይወት ዙሪያ የሚሠራውን ነገር መስማማታቸውን ሲገልጹ ወ/ሮ ታደለችም ድምጻቸውን ከፍ አድርገው "አሜን" አሉ።

"ምነው አጥብቀሽ አሜን አልሽ?" አሉ ኬዳሞ ከጸሎት በኋላ። "የጸለይከው የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን ብለህ አይደል?" ብለው ጥያቄያቸውን በጥያቄ መለሱ ወ/ሮ ታደለች። በእግዚአብሔር ፈቃድ መስማማት እንዳለባቸው ሁለቱም ተስማምተው ጉዳዩን ዘጉ።

ባል እና ሚስት ሰኞ ማለዳ በአስራ አንድ ሰዓት ተነስተው እንደገና ጸለዩ። የእግዚአብሔርንም ቃል አንብበው ተነሱ። በዚሁ ጊዜ ወንጌላዊው የቡታጅራ ጉዞ ያደከመው ሰውነታቸውን በደንብ ለማሳረፍ ወደ አልጋቸው ሲመለሱ ወ/ሮ ታደለች "ሰራተኛን እኮ ሰው ሞቷል። ለምን ሄደህ ድንኳን በመትከል አትረዳም?" አሉ ባለቤታቸውን። በዚህ ጊዜ ጉዳዩን ረስተው የነበሩት ኬዳሞ "ለዚህ እኮ ነው ሁሌ እንድትኖሪልኝ የምፈልገው እኔ ረስቼው ነበር።" አሉአቸው እና ባል እና ሚስቱ ተሳሳቁ። ኬዳሞም ወደ ለቅሶ ቤት ሄዱ። በዚያውም ወንደሰን ኃይሉ የሚባል የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ሠራተኛ የሆነ ወጣት ለባለቤትዎ ብሎ የገዛላቸውን አፕል ሲቀበሉ ወደ ዋና ጽሕፈት ቤት ሄዱ። ወንድወሰን አፕሉን የገዛው ዓርብ ዕለት ቢሆንም ወንጌላዊው ወደ ቡታጅራ ይሄዱ ስለነበር ዓርብ ዕለት ሊወስዱ እንደማይችሉ ነግረውት ጥበቃ ሠራተኞች ቢሮ እንዲያስቀምጥላቸው አደራ ባሉት መሠረት ከጥበቃዎች ቢሮ ሄደው ወሰዱ።

ኬዳሞ ወደ ቤት እንደተመለሱም ወደ ባለቤታቸው መኝታ ክፍል ሲገቡ ወ/ሮ ታደለች ከአልጋ ተነስተው ሶፋ ላይ ተቀምጠው አልጋውን በቤት ያሉ የወ/ሮ ታደለች ረዳቶች የሆኑ ሁለት ልጆች እያነጠፉት ነበር። ከዚያም ወንጌላዊው ያመጡትን ሁለት ኪሎ አፕል ሁለት ቦታ ከፍለው አንዱን ለባለቤታቸው ሰጡአቸው እና ይህ ያንቺ ነው፣ ይህኛው ደግሞ የእኔና የጋብቻ ወልድ ነው ብለው ወደ ልጃቸው ክፍል ሄዱ። አፕሉን ልጃቸው ክፍል አስቀምጠው ሲመለሱም ቀና ብለው ሲያዩአቸው ወ/ሮ ታደለች ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ውብ ሆነው ስለ ታዩአቸው "አንቺ እኮ አሁንማ ሙሽሪት ሆነሻል።" አሉአቸው። ወ/ሮ ታደለች በመገረም ሲያዩአቸው "እውነቴን እኮ ነው፣ ለምን ሙሽሪት እንደምትመስዪ አላውቅም በጣም ተውበሻል።" አሉ። በዚሁ ጉዳይ ባል

*እና ሚስት እየተቀባለዱ ሲሳሳቁ ቆዩ እና ኬዳም አንዳንድ ነገር ለመሥራት በቤታቸው ውስጥ ወዳደራጁት ቢሮአቸው ገቡ።*

*ከጥቂት ጊዜ በኋላም ኬዳም ቀና ብለው ሲያዳምጡ ባለቤታቸው ክፍል ከነበሩት ልጆች አንዷ ድምጿን ከፍ አድርጋ "እትዬ ... እትዬ" ትላለች። ወንጌላዊው ሄደው ሲመለከቱ ወ/ሮ ታደለች ምንም ምላሽ አይሰጡም። ራሳቸውን እንደሳቱ ሲያዩም እዚያው አልጋ ላይ ሄደው አንስተው አቀፉአቸው። ከዚያም ምንም የማይሰሟቸውን ባለቤታቸውን እንዳቀፉ ለአጭር ጊዜ ሲጸልዩ ቆዩ። በኋላም የወ/ሮ ታደለችን አስከሬን በአልጋው ላይ አስተኝተው ተነሱ። ያቺ ደቂቃ በወንጌላዊው ሕይወት ታላቅ ጨለማ የሰፈነባት አስጨናቂ ጊዜ ሆነች። ካሉበት ተነስተውም ወደ የመጨረሻ ልጃቻው ምህረት ጋ ስልክ ደወሉና በፍጥነት ወደ ቤት መጣች።*

*በዚህ ጊዜ ወንጌላዊው በውስጣቸው የሚሰማቸው ባዶነት ከፍ እያለ ሄደ። ከራሳቸው ጋርም "እርሷስ ወደ ገነት ወደ ጌታዋ ሄደች፤ ታዲያ እኔ ምንድን ነው የምሆነው?" እያሉ እየተነጋገሩ በከባድ ጨለማ ውስጥ እንዳሉ ይሰማቸው ጀመር። ልክ በዚህ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ላይ እያሉ መንፈስ ቅዱስ "ጸልይ!" ሲላቸው ተሰማቸው። ወዲያውኑ በኃዘን ግራ ተጋብተው እያለቃቀሱ የነበሩትን ልጃቸውን ምህረትን እና ባለቤታቸውን ሲረዱ የነበሩትን ሁለት ልጆች ይዘው ለጸሎት ተንበረከኩ። አራቱ ተንበርክከው እየጸለዩ እያለም በዮሐ. 16፡33 ላይ የተጻፈው "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ። ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌአለሁ።" የሚለው ቃል ላሉበት ሁኔታ መልእክት ሆኖ መጣላቸው። መንፈስ ቅዱስም 'የተሸነፈው አላሸነፈህም።' አላቸው። ወንጌላዊውም እዚያው "ብቃ ሰይጣን ተሸንፎአል፤ ሞት ተሸንፎአል። በክርስቶስ የትንሳኤ ኃይል ድል ሆኖአል።" ብለው የትንሳኤው ኃይልን መንፈስ ተላብሰው ተነሱ። በዚያችው ቅጽበትም በውስጣቸው ሊሰማቸው ጀምሮ የነበረው የሞት መንፈስ ከውስጣቸው ጠፋ። ሞት ከእግራቸው በታች እንደሆነ ታወቃቸው። የሞትና መውጊያው የሲኦልና ድል መንሳቱ ክፉ መንፈስ በኃያል ንፋስ እንደተገፋ ደመና ከውስጣቸው በነው ጠፋ።*

.................//..................

## "ትለመልማለህ!"

ከዓመታት በፊት ታደለችን ካገባኋት በኋላ ሁለታችን የኖርነው ፍጹም ክርስቲያናዊ ትዳር ነበር። በጣም አስተዋይና ራሷን የምታስተምር ሴት ስለነበረችም በገጠርም ሆና በከተማ ኑሮአችንን ጥሩ አድርጋ ለመምራት አልተቸገረችም ነበር።
ልጅ በምትወልድበት ጊዜ እንኳን ከአገልግሎት እንዳልቀር የምታበረታታ የእምነት ሰው ነበረች። በልጆች አያያዝም ጎበዝ ስለነበረች ከእርሷ በፊት ከብዙነሽ በተወለዱት ልጆቻችን የተነሳ እንኳን እኔ አልተቸገርኩም ነበር።

የመጀመሪያ ልጁ ዳዊት በአደጋ ሕይወቱ እስካለፈበት ጊዜ ድረስ ለኔም ለእርሷም ልጅ ሆኖ የኖረ ሲሆን እርሷ ሳትመጣ በፊት ጀምሮም በአያቷ ቤት መኖር የጀመረችውን ድንቅነሽን እንኳን ከእኛ ጋር እንድትኖር ለማድረግ ብዙ ጥራ ነበር። በአንድ ወቅት እንደውም እኛ በምንኖርበት ቦቢቾ ከኛ ጋር እየኖረች እንድትማር ስጦታ ሁሉ አዘጋጅታ ጋቢ ገዝታ ሻሸን ድረስ ሄዳ ብትለምናትም አያቷን መርጣ "ያሳደገችኝን እናቴን ጥዬ አልሄድም" ብላ ፈቃደኛ ሳትሆን ቀርታለች።

የድንቅነሽ ነገር ለኔም ችግር እንደሚሆን በማሰብ ከእኛ ጋር ወደ ከተማ እንድትመጣ ለማድረግ እኔም ጥሬ የነበረ ቢሆንም ሳይሳካልኝ ቀርቷል። ልጄ ድንቅነሽን ገና ድሮ "ወደ እኛ ነይ አለዚያ ያንቺ ነገር ወደ ፊት ለእኔም ቋሚ ችግር ይሆናል።» እንዳልኳት አሁንም እኔም የምቸገርበትን የገጠር ሕይወት እና ኑሮ በሻሸን ትገፋለች። በእርግጥ በገጠር ከአያቷ ጋር ኖራ ተድራ ብትወልድም የወለደችው ወርቅነህ የተባለ የልጅ ልጄ ራሱ አድጎ የራሱን ልጅ ወልዶ ቅድመ አያት አድርጎኛል። ሆኖም የኑሮአቸው ሁኔታ ግን እስካሁን ድረስ የሌላ ሰው ድጋፍ የሚፈልግ የተጻከመ ነው።

ወደ ውዷ ታደለች ትረካዬ ልመለስ ታደለች በነበረን የትዳር ሕይወት የወለደቻቸውን ስድስት ልጆች በሚገባ ተንከባክባ ማሳደግ ችላለች። የምናገኘው ገቢ በጣም አነስተኛ ቢሆንም አንድም ቀን ሳንቸገር (ሳንራብ) መኖር ችለናል። በተለይ ማረቆ በነበርንበት ጊዜ ከክፍለ ማኅበራችን የሚላክልን 30 ብር የወር ደመወዝ ብቻ ስለነበር ሁኔታው አስቸጋሪ ነበር። ነገር ግን ታደለች እና እኔ ገንዘቡን ከማውጣታችን በፊት ቁጭ ብለን ለቀናት ከመከርን በኋላ ጥቅም ላይ ስለምናውለው ሳንቸገር ኖረናል። ያኔ በመጀመሪያ 30 ብራችንን ይዘን እንቀመጥ እና የአሥራት 3 ብር እና ለአስፈላጊ ነገሮች 10 ብር ተቀማጭ ለይተን በማስቀመጥ በ17 ብሩ ወር ሙሉ ሊያቆየን የሚችል ነገር ምን እንደሆን እናሰላለን።

ከዚያም ረከስ ያሉ ምግቦችን እንደ የበቆሎ ቂጣ ያለውን በቡና እና በሻይ እየበላን፣ ስጋ ባናገኝም አንዳንድ ጊዜ አይብ እና ሽሮ እየተመገብን እንኖር ነበር። ያኔ ሁለታችንም ተግባብተን ዓላማችን አገልግሎቱ ላይ ስለነበረ ምን በላን ብለን አንጨነቅም ነበር። ታደለች በዚህ መልኩ በችግር ጊዜ እንኳን ቤታችንን እየመራች አንድ ቀን ገንዘብ አለቀ ብለን ብድር ፍለጋ ሳንሄድ በሰላም ኖረናል።

በአዲስ አበባም ታደለች የቤቱን አስተዳደር ሙሉ በሙሉ ቀጥ አድርጋ ይዛ የሚያስፈልገውን ሁሉ እያደረገች ጥሩ ኑሮ እንድንኖር ማድረግ ችላለች። ከዚህም አልፋ ከብቶች አርብታ ወተት እየሸጠች ኑሮአችንን የደገፈች ሲሆን ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ቃለ ሕይወት ለአገልግሎታችን የመስክ ወጪ መሸፈን ባልቻለችበት ጊዜ ለአገልግሎቱ ድጎማ እየሰጠች እንዳገለግል አድርጋለች። በትጋቷ የኔ አገልግሎት የተሳካ እንዲሆን ትልቅ ሥራ የሠራችና በምሳሌ ምዕራፍ 31 ላይ እንደተጠቀሰችው ሴት ለቤታችን የሚያስፈልገውን ሁሉ ተቆጣጥራ ቤቱን እስከ ዕለተ ሞቷ ታስተዳድር የነበረች ብርቱ ሴት ናት።

እኔም ይህቺን ዓይነቷን የመንፈሳዊ እና ስጋዊ ሕይወት አጋሬን ስላጣሁ ነበር ሕይወት ከእርሷ ሞት በኋላ ጭልም ብሎ የታየኝ።

የእግዚአብሔር መንፈስ በጊዜው በቤታችን የገባው ሞት የፈጠረብኝን ስሜት ሊያስወግድ "የተሸነፈው አላሸነፈህም" ብሎ ከተናገረኝ በኋላም አስፈላጊውን የቀብር መሰናዶ ለመፈጸም ተነሳሁ። ወዲያው የጌጃ ኅብረት አጋሮቼ ወደ ሆኑት አቶ ወልደ አምላክ እና አቶ ደምሴ ስልክ ደውዬ ነገርኳቸውና እነርሱም ፈጥነው መጡ። ከእነዚህ አንጋፋ ወዳጆቼ ጋር በመሆንም የሚያስፈልገውን ሁሉ በጋራ ተወያይተን እቅድ አወጣን። ወዲያውም የሰማው ላልሰማው እያሰማ ሰው ሁሉ ተሰባሰበ።

የቀብር ስነ ስርዓቱም በጌጃ ኅብረታችን፣ በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት እና በሌሎችም ትብብር በጥሩ ሁኔታ ተካሄደ። ምንም እንኳን የታደለች ከእኔ መለየት የኔም መጨረሻ እንደመጣ የሚያስመስል ነበር። በዚያ ጊዜ የኔ ዕድሜ ራሱ ወደ ሰማንያ የተጠጋ ስለነበር ሁሉም ነገሬ እያከተመ ያለ ቢመስልም እኔ ግን በጽናት ለመቆም ቻልኩ። ባለቤቴ ታደለች ሰኞ ዕለት አርፋ ማክሰኞ ቀን የቀብር ስነ ሥርዓት ተካሄደ። በዕለቱ እኔም በዮሐንስ ወንጌል 3፡16 ላይ ባለው ሃሳብ ላይ የተመሠረተ መልዕክት አቀረብኩ። "በእርሱ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወድዶአልና" እንደሚል ቃሉ የሁላችን እምነት መሠረት የዘለዓለም ሕይወት እንደሆነና እግዚአብሔርም ያንን ሕይወት በልጁ በኩል እንደሰጠን ተናገርኩ።

"ታደለችም ከትናንትና ጀምራ አዲስ ሕይወት ጀምራለች።" በማለት ለ60 ዓመታት የሰበክሁትን የዘለዓለም ሕይወት ተስፋ አበሰርኩ።

ከዚያ በኋላም ከያዝኳቸው ፕሮግራሞች የሰረዝኩት በቀብሩ ማግስት ከእሮብ ጀምሮ በመቀሌ ይካሄድ የነበረውን የቤተ ክርስቲያናችን ጠቅላላ ጉባኤ ላይ መገኘትን ብቻ ነበር።

ታደለችን ቀብረን ብቻዬን ለመጀመሪያ ጊዜ በባዶው መኝታ ቤቴ ገብቼ ተኛሁ። እንደ ልማዴም ከሌሊቱ 8 ሰዓት ላይ ተነስቼ ከአልጋዬ ወርጄ ተንበርከኬ። እስከ ዛሬ ወደ ሰማኝና ወዳልተለየኝ አምላኬም ልመናዬን አፈሰስኩ። በውስጤ የሚሰማኝን ሃዘንና ብቸኝነት በማሰብም በእምባ በታጀበ ልመና "ጌታ ሆይ እስከ ዛሬ ድረስ እርሷን ሰጥተኸኝ ለ49 ዓመታት አንተ ባሸከምከን ቀንበር ውስጥ ገብተን ስናገለግልህ ኖረናል። አሁን ግን እርሷን ወሰድካት። ከእንግዲህ በቀንበሩ ውስጥ በእርሷ ፈንታ አንተ ካልገባህ እኔ ብቻዬን አልችልምና አንተ በማቴዎስ 11፡28 ላይ "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔ ተማሩ" ብለህ የለ? አሁን እኔ ብቻዬን አልችልምና ከአንተ ጋር መሆን እፈልጋለሁ።" እያልኩ ጸለይኩ። ከዚያም በእግዚአብሔር ፊት ያፈሰስኩትን እምባ እያባበስኩ ተነስቼ ተኛሁ።

እንደተኛሁም ገና እንቅልፍ እንደወሰደኝ ራእይ አየሁ። በራእዩ ውስጥ በመጀመሪያ የለመለመ ከዚያም በደንብ ያበበ ቀጥሎም ፍሬውን ያንዠረገገ በቆሎ አየሁ። ይህ ምንድነው ብዬ ስጠይቅም መንፈስ ቅዱስ "አንተ ገና ትለመልማለህ፣ ታብባለህ፣ ብዙ ፍሬም ታፈራለህ።" ብሎ መለሰልኝ። በእውነትም ውስጤ ታድሶ እንደገና ለአገልግሎት ተነቃቅቼ ተነሳሁ። በእነዚያ ሰሞናትም በየቦታው ቃሉ እየተሰበከ እንደተለመደው የኮንፈረንስ ጊዜ ሆኖ የለቅሶው ጊዜ ተጠናቀቀ።

## መለምለም

ታደለች ከሞተች በኋላ እግዚአብሔር የሰጠኝን የተስፋ ቃል ይዤ እንደገና አገልግሎቴን ቀጠልኩ። አስቀድሜ በጀመርኩት እና እግዚአብሔር በብዙ አቅጣጫ እየተጠቀመበት በነበረው የአገልግሎት ስልት መሠረትም ማገልገሌን ቀጠልኩ። ይሁንና በጊዜው ሴት ልጆቼ በሙሉ አግብተው ከቤት ስለወጡ የነበረውን የጓዳ አስተዳደር ታደለችን ተክቶ የሚያከናውን ትክክለኛ ሰው ስላልነበር ለኔ የማይመች ሆኖ ነበር።

በዚሁ ሁኔታ ውስጥ እያለንም ታደለች በሞተች በ10ኛው ወሯ ላይ ከኔ የትውልድ አገር ሦስት ትልልቅ ሰዎች መጥተው በዚህ እድሜዬ ብቻዬን መኖር እንደሌለብኝ እና ትዳር መመስረት እንዳለብኝ መከሩኝ። "ታደለችን አስር ዓመት አስታመሃታል። አሁን እርሷ ሞታለች፤ ያንተም ዕድሜ ገፍቷል። ብቻህን ሠራተኛ የሚሰጥህን እየተመገብህ መኖር አይመችህም። አገልግሎትህን መቀጠል እንድትችል ምቹ የሚሆነው ስታገባ ነው።" አሉኝ።

እኔም "በመጀመሪያ ይህን የማስብበት ጊዜ አልደረሰም። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ነገሩን ለመወሰን እግዚአብሔርን መጠየቅ እና ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋርም መመካከር አለብኝ። እንዲሁም ከልጆቼ ጋር ተነጋግሬ መስማማት አለብኝ" አልኳቸው። ነገር ግን በጉዳዩ ላይ ፈቃደኛ ሆኜ እንደምጸልይበት ነግሬአቸው ሄዱ። እኔም ነገሩን ልጸልይበት ማስታወሻ ደብተሬ ላይ ጻፍኩት። ልጸልይበት ባልኩት መሠረት ለመጸለይም ወደ እግዚአብሔር ከባዱን አጀንዳ ይዤ ቀረብኩ። እናም "እግዚአብሔር ሆይ ብቻዬን መኖሬም አስቸጋሪ ነገር ነው። ሳግባ ብል ደግሞ ማግባትም አስቸጋሪ ነው። ያንተ ፈቃድ በዚህ ውስጥ ምን እንደሆነ ግለጥልኝ?" ብዬ ጸለይኩ።

በዚህ ጊዜ ሚስት ማግባት ለእኔ ችግር የሆነበት ምክንያት የመጀመሪያው የዕድሜዬ ሁኔታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከጤናዬም አንጻር ራሱ ስኳር እና ደም ግፊት ጀምሮኝ ስለነበር ነው።

"ይህንን የኔን አስቸጋሪ ሁኔታ አይታስ የትኛዋ ሴት ተቀብላ ታገባኛለች (ባሏ ታደርገኛለች)?" እያልኩ  አስብም ነበር። ለማንኛውም በነገሩ ላይ ልጸልይበት በተስማማሁት መሠረት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ እየጸለይኩ ቆየሁ። በነገሩ

ላይ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ማሰብ ጀምሬም የማገባ ከሆነ የማገባት ሴት ማሟላት ያለባትን ስድስት ነገሮች ዝርዝር መመዘኛ አውጥቼ ያዝኩ። ለሦስት ወራት ያህልም በነገሩ ላይ ስጸልይ ቆይቼ እኔ ያሰብኳት ሴት ልትመጣ ስላልቻለች ተስፋ ወደ መቁረጥ ሄድኩ።

ሙሉ በሙሉ ተስፋ ቆርጬ "በቃ ይህ ነገር የሚሆን አይደለም" አልኩና በዚህ ጉዳይ ላይ ዳግም ላለማሰብ "ነገሩን ዘግቻለሁ" አልኩና መጸለይ አቆምኩ። ነገር ግን እኔ አርብ ቀን ይህንን ውሳኔ ወስኜ ቅዳሜ ማታ ላይ የግል ጸሎቴን እየጸለይኩ እያለ እግዚአብሔር "ኬዳሞ ባንተ ጉዳይ ላይ እኔ አያገባኝምን?" ብሎ ተናገረኝ። እኔም አሁንም ነገሩ ይሆናል የሚለው ሃሳብ ሊታየኝ ስላልቻለ እግዚአብሔር እንደፈቀደ ይሁን ብዬ በተከፈለ ልብ ተስማምቼ ፈጽሞ የዘጋሁትን በር ገርበብ አድርጌ ከፈትኩ። ነገር ግን በዚህ ሁኔታዬ ያልተደሰተው እግዚአብሔር "ለእኔ ኃላፊነቱን ከፍለህ ነው የምትሰጠኝን?" በማለት እሁድ ማታ ተናገረኝ።

እኔም ሁሉ እንደ እርሱ ፈቃድ የወደደው እንዲሆን ተስማምቼ ሁሉን ለእርሱ በመተው እንደገና መጸለዬን ቀጠልኩ።

በዚሁ ነገር ዙሪያ አብረውኝ የሚጸልዩም ነበሩ። ጊዜው ሄዶም በ2002 ዓ.ም አንድ ዓርብ ቀን ከአቶ ደምሴ ማዴ ጋር በኔ የትዳር ጉዳይ ላይ እየጸለይን ነበር። በመጨረሻም ተስፋ ቆርጬ አቶ ደምሴ "በዚህ በማይሆን ነገር እግዚአብሔርንም፣ አንተንም፣ ራሴንም ማስቸገር የለብኝም። በቃ አይሳካምና ጸሎቱን እናቁም።" አልኩት። እርሱ ግን "አግባም አታግባም" ሳይል መጸለያችንን መቀጠል እንዳለብን ሃሳቤን እንዳልለውጥ ነገረኝ እና በነገሩ ላይ ለረጅም ጊዜ ተወያይተን ተለያየን።

ይህንን ተነጋግረን በተለያየንበት በዚያ ዓርብ ቀን ምሽት ላይም እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተምራ በዲፕሎማ የተመረቀች ቀጭን ጠይም ሴት አሳየኝ። ቅዳሜ በማለዳ እንደተነሳሁም ለአቶ ደምሴ ደውዬ ያየሁትን ነገርኩት። እርሱም "አንተ ቸኩለህ ነው እንጂ እግዚአብሔር መቼ አይሆንም ብሎ ዘጋው?" አለኝ።

ይህ ነገር በተፈጸመ በሁለተኛው ቀን ሰኞ ዕለትም ለአገልግሎት ወደ ሆሳዕና ሄድኩና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ሳስተምር ቆየሁ። በኋላም እዚያ ለነበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር እና የአስተዳደር ኃላፊ "ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በዲፕሎማ ተመርቃ እያገለገለች ያለች ሚስት ልትሆነኝ የምትችል ሴት ፈልጉልኝ።" አልኳቸው። (በጊዜው እኔ ያወጣሁትን መስፈርት የምታሟላ መሆን እንዳለባትም ገልጬላቸው ነበር።) በቢቾ በነበረኝ ቆይታ ማክሰኞ ዕለትም እንዲሁ እየጸለይኩ እያለሁ ያቺው ጠይም ሴት አልጋዬ ላይ ከአጠገቤ ተቀምጣ አየሁ። ጸሎቴን ከጨረስኩ በኋላም "ይህቺን ሴት አሁን የትኛው ዓለም ላይ ሄጄ ነው የማገኛት?" አልኩ።

ፊልጉ ብዬ የነገርኳቸው ሰዎችም ወደ አዲስ አበባ ከመመለሴ በፊት ሐሙስ ቀን ልጅቷን ሊያገኙ እንዳልቻሉ ነገሩኝ። እኔም አዲስ አበባ መጥቼ በጣም ለሚወዱኝ እና የቅርቤ ለሆኑ ሁለት ሴቶች ጉዳዩን አማከርኳቸው። ነገሩን ከሰሙት ሁለት ሴቶች አንዷ ወዲያው "ይህቺማ በሌ ያለችው አልማዝ ናት!" አለች። እኔም አልማዝን አውቃት ስለነበረ ሄጄ አናገርኳት። እርሷም በነገሩ ተስማማች።

ከጥቂት ጊዜ ቆይታ በኋላ ግን በውሳኔዋ ለመጽናት ተቸገረች። አንድ ቀንም "ልጆችህ ወደ እኔ ሰው እየላኩ ተይ እያሉኝ ነው።" አለችኝ። እኔም "እይ ይህ እኔን ከልጆቼ ጋር ማጣላት ነው። አንቺ የማትፈልጊ ከሆነ ይቅር በዚና መጋባታችን ይቀራል።" ብዬ ወደ ቤቴ ሄድኩ።

ከእርሷ ጋር ይህንን የተነጋገርነው ማክሰኞ ቀን ሲሆን እኔም በነገሩ እንደገና ወደ ተስፋ መቁረጥ ሄድኩ። ነገሩ አንደኛ ከልጆቼ ጋር ሊያጣላኝ ነው። በዚያ ላይም ሁኔታው ተስፋ አስቆራጭ ሆነ ብዬ አሰብኩ። አስጨናቂ ሁኔታ ላይ ስለነበርኩ ስኳሬም ደሜም ከፍ አለ። እንደልማዴም በሕይወቴ የሚገጥመኝን ፈተና ሁሉ ሁል ጊዜ እያሳለፈኝ ወደ ረዳኝ አምላኬ መጸለዬን ቀጠልኩ።

አንድ ዓርብ ማታም ሌሊት በ9 ሰዓት ተነስቼ ከጸለይኩ በኋላ ተመልሼ ተኛሁ። ወዲያውም በህልሜ ሁለት ሴቶችን ሲያመጡልኝ አየሁ። አንዷት ቀይ፣ ረዥም፣ መልከ መልካም ሴት እና አንዷት ጠይም፣ ቀጭን ሴት።

እኔም በቢቶ ያየኋት የትኛዋ ነች? አልኩ እና ጠይሟን እንደሆነ አስታወስኩ። "በቃ ይህቺ ከእግዚአብሔር የተሰጠችኝ ባለቤቴ ናት" አልኩ ለራሴ።

# ምዕራፍ ፵፫

# ሠላም ተገኘች

## ሦስተኛው ሠርግ

*ወንጌላዊ ኬዳሞ የሰምንት አስርት ዓመታት ዕድሜን ካስቆጠሩ በኋላ በቀረው ዘመናቸው ወንጌልን እያገለገሉ ለመቀጠል እንደገና ትዳር መያዝ እንዳለባቸው አምነው ቢራመዱም መንገዱ ቀና አልሆን ብሏቸው ተቸግረዋል፡፡ የትዳር ምስረታው ሃሳብም ከግራ እና ከቀኝ ደጋፊ እና ተቃዋሚ አላጣም፡፡*

*በወቅቱ ኬዳሞን እና አገልግሎታቸውን የሚያውቁ የወንጌላዊው የቅርብ ሰዎች አገልግሎታቸው እንዲቀጥል እና ሩጫቸውን በድል እስከ መጨረሻው እንዲያጠናቅቁ የሚመኙ የትውልድ አገራቸው ሰዎች፣ የጌጃ አጋሮቻቸው የነበሩት አገልጋይ መሪዎች እና ቤተሰቦች፣ የኬዳሞ አጥቢያ መካኒሳ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ጨምሮ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ አካላት እና መሪዎች ኬዳሞ "በ80 ዓመታቸው ማግባት አለባቸው ወይስ የለባቸውም?" በሚል ጥያቄ እና ሙግት በየቦታው ተነስቶ መወያያ ሁሉ ሆኖ ሰነበተ፡፡ በዚያ ላይ ኬዳሞ ባለ ስድስት ነጥብ መመዘኛ ያዘጋጁላት ሴት በቀላሉ ልትገኝ አልቻለችም፡፡*

*ይሁንና ወንጌላዊው ለስድስት አስርት ዓመታት ያገለገሉት አምላካቸው በባለቤታቸው ቀብር ዕለት ማታ እንደገና እንደሚያለመልማቸውና እንደገና እንደሚያፈሩ ተናግሯቸው አገልግሎታቸውን ቀጥለዋል፡፡ የትዳር መያዙ ነገር አስጨናቂ ሆኖባቸው ተስፋ ቆርጠው በር ሲዘጉም ጌታ ተው ብሎ ጸሎት አስቀጥሏቸው የሚያገቧትን ቀጭን፣ ጠይም፣ መጽሐፍ ቅዱስ የተማረች ሴትም በራእይ አሳይቷቸዋል፡፡*

*አንድ ቀን አንድ ከኬዳሞ ጋር ዝምድና ያለው ወጣት ወደ እርሳቸው ቀርቦ ስለ አንዲት ከበቡሽ መክሮ ስለምትባል ቀጭን ጠይም መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተምራ የተመረቀች ልጅ አጫወታቸው፡፡ ኬዳሞም ይህቺን ልጅ ካዘጋጁት መመዘኛ አንጻር በመገምገም 'አንዱን መስፈርት አታሟላም' አሉ፡፡ በጊዜው ሴቲቱ ያላሟላችው የኬዳሞ መስፈርት ዕድሜዋ ከ50 ዓመት በታች መሆኑ ነበር፡፡ ስለሆነም ኬዳሞ ከ50 ዓመት በታች የሆነች ሴት ፍላጎቷ ብዙ ስለሚሆን መጋባቱ ለእርሳቸውም ለእርሷም ችግር*

*እንደሚሆን ተናገሩ። ያ ወደ ኬዳሞ የመጣው አስተዋይ ሰውም "ዕድሜዋ ከ50 ዓመት በላይ የሆነ የኛ ሃገር ሴት መቼ ትዳር ትፈልጋለች? ጋሼ ኬዳሞ ይህንን ሁኔታስ እንዴት ረሱት?" አላቸው። ከበቡሽ ዕድሜዋ አርባ ሊሆን እንደሚችል፣ ባሏ እንደሞተባት ልጅ እንደሌላትም ነገራቸው።*

*በኋላም ከበቡሽ ወደ ሆሳዕና መጥታ ከኬዳሞ ጋር ተዋወቀች። ጊዜ ወስደው ተነጋገሩና ለመጋባትም ወሰኑ።*

*ሰኔ 2 ቀን 2002 ዓ.ም ኬዳሞ ከአዲስ አበባ ሆሳዕና ሄደው አደሩ። የኬዳሞ ቤተሰብ እና የከበቡሽ ቤተሰብ የሆኑ ሰዎችም ከሻሸነ መጥተው ሆሳዕና አድረዋል። ሆሳዕና በገቡበት ዕለትም የሥርጉ እና የቃል ኪዳኑን አፈጻጸም ሁኔታ ተነጋግረው ጨረሱ።*

*ሰኔ 3 ሐሙስ ዕለትም ሆሳዕና ከተማ ሞቢል በሚባል ሆቴል ፎቅ ላይ በሚገኝና ለሌሎች ቤተ ክርስቲያናት መሰብሰቢያና በአምልኮ አዳራሽነት የሚያገለግል አዳራሽ ውስጥ ከ30 በላይ ምስክሮች በተገኙበት የጋብቻ ሥነ ስርዓቱ ተካሄደ። ወንጌል ተሰብኮ መጋቢ አላምረው የኬዳሞ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሆነችው የመካኒሳ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን በመወከል ቃል ኪዳኑን አስፈጸሙ። የጋብቻ ስነ ሥርዓቱ ከተጠናቀቀ በኋላ የተሰናዳውን ድግስ እድምተኞቹ ተቋድሰው ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ሆነ። ኬዳሞም ለሦስተኛ ጊዜ ተሞሽረው ባለ ትዳር ሆኑ። እግዚአብሔር በስተ እርጅና የሰጣቸውን ሚስትም ሰላም ብለው ሰየሟት።*

--------------------------------//--------------------------------

# እንደገና አፈራሁ

ሐሙስ ዕለት ጋብቻዬን ከመፈጸሜ በፊት ከከበቡሽ መከሮ ጋር ተገናኝተን ተነጋገርን። እኔም ስለ ራሴ ሁኔታ ነገርኳት። እርሷንም ጌታን ምን ያህል እንደምትወድና የበፊት ሕይወቷ ምን ዓይነት እንደነበረ ጠየቅኋት። እርሷም ጌታን በጣም እንደምትወድ በቤተ ክርስቲያንም እንደምታገለግልና ወደፊትም አገልግሎት መቀጠል እንደምትፈልግ ነገረችኝ። እኔም እግዚአብሔር በራእይ ያሳየኝ ጠይም ቀጭን ሴት እርሷ መሆኗን አምኜ ለጋብቻ ጠየቅኋት እና ለመጋባት ተስማምተን ቀጠሮ ይዘን ተለያየን።

ይህንኑ የጋብቻዬን ሁኔታም እኔን ለሚያውቁ ለብዙ ሰዎች እና ሽማግሌዎች አሳወቅሁ። በዚሁ ጊዜ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የማግባት ውሳኔዬን አጥብቀው ተቃወሙት። እኔም "ለምን? ማግባት አልችልም?" ብዬ ስጠይቃቸው እኔ ካገባሁ በአዲስ አበባ ረዥም ዘመን የኖሩ ባለትዳሮች ሚስት ወይም ባል ሲሞትባቸው እንደገና ማግባት ብዙም የተለመደ ባህል ስላልሆነ አገልግሎቴን ለመቀጠል እንደሚያስቸግረኝ ነገሩኝ። እኔም መጽሐፍ ቅዱስስ ምን ይለኛል? ብዬ ስጠይቃቸው መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንደማይከለክለኝ ተናገሩ። እኔም "ታዲያ የቱን ልከተል? የአዲስ

አበባን ባህል ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት?" ብዬ ማግባቴ ትክክል እንደሆነ ተናገርኩ። የኔ አጥቢያ ለሆነችውና ቢጋብቻዬ ጉዳይ ላይ በተለይ የመወሰን ስልጣኑ ላላት የመካኒሳ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም የማግባት ጥያቄዬን አቀረብኩ።

የቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎችም ላቀረብኩት የጋብቻ ጥያቄ እሺ ብሎ መወሰን ከበዳቸው። እኔም እነርሱ ጋ ቀርቤ ውሳኔዬ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ለማስረዳት ሞከርኩ። እያንዳንዳቸውን በግል እናግሬ ለማሳመንም ጣርኩ። በተለይ ከሽማግሌዎቹ አንደኛው አምስት ጊዜ ያህል እያገኘኝ "እንዴት ታገባለህ?" ብሎ ማግባቴ ትክክል እንዳልሆነ ለማሳመን ሞከረ።

ለመጨረሻ ጊዜ ከሽማግሌዎቹ ጋር ቀርቤ ስነጋገር ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር የሚከለክለኝ ምንም ነገር እንደሌለ ስላመኑ ጠንከር አድርጌ ተናገርኳቸው። "ለካስ እናንተ መጽሐፍ ቅዱስን የማታውቁ እና የማትታዘዙ ዓለማውያን ሽማግሌዎች ናችሁ። የምትታዘዙት እና የምትመሩት መጽሐፍ ቅዱስን በመከተል ሳይሆን በዓለም ባህል እና ልማድ ነው። እኔንም የምትከለክሉት በመጽሐፍ ቅዱስ ታዝዛችሁ ሳይሆን በባህል እና ልማድ ተይዛችሁ ነው።" አልኳቸው።

በመጨረሻም በተደጋጋሚ ሲማከሩ ቆይተው ተስማሙ እና ጋብቻውን ፈቀዱልኝ። በቤተ ክርስቲያን አማካኝነትም ቃል ኪዳኑ እንዲካሄድ ተስማማን።

የጋብቻዬን አስፈላጊነት የእግዚአብሔርም ፈቃድ መሆኑን ልጆቼንም እንዲሁ ሰብስቤ አነጋግሬ ተማምነንበት ነበር። በተነጋገርንበት ጊዜ ሁሉም በነገሩ መደሰት ባይችሉም አስፈላጊ እንደሆነ አምነው ተስማምተን ተለያየን። ከቆይታ በኋላ ግን አንዳንድ የኔን ማግባት የሚቃወሙ ሰዎች ለአንዷ ልጄ "በእናትሽ ቦታ እንዴት ሌላ ሴት ትገባለች?" ብለው ጥያቄ ፈጥረውባት መጥፎ እንክርዳድ ስለዘሩ "አንተ ብቻህን መኖር የለብህም" ስትለኝ የነበረችው ልጄ ተመልሳ የሀሣቡ ተቃዋሚ ሆነች።

ወደ መጨረሻ ግን እርሷም ተስማምታ ለሠርጉ ሁሉ ዝግጅት ወደ ማድረጉ ገባች። እኔም ይህንን የሕይወቴን ከባድ ምዕራፍ ለመዝጋት ነገሮችን በጥንቃቄ ለማድረግ ወሰንኩ። አስቀድመን ከማገባት ልጅ ጋር በተነጋገርነው መሠረትም ሠርጉ ሆሳዕና እንዲሆን አደረግሁኝ።

ከሠርጉ በፊትም ሐሙስ ዕለት ሠርጉን ሆሳዕና ከማካሄዳችን በፊት ሰኞ ቀን የኔ የቅርብ ሰዎች ለነበሩት ለነ አቶ ደምሴ ማዴ፣ ለዶ/ር ሙላቱ ባፋ፣ ለአቶ ሽፈራው ወ/ሚካኤል፣ ለአቶ ወልደ አምላክ ዲኬ በአጠቃላይ አምስት ቤተሰብ ጠርቼ የሠርጉን ሁኔታ ነገርኳቸው። ልጆቼንም ሰብስቤ ስለ ሠርጉ አሳውቄ የእነርሱ መገኘት እንደማያስፈልግም ተማምነን እኔ ወደ ሆሳዕና አመራሁ።

ሆሳዕና ከተማ ላይ የሠርግ ሥነ ሥርዓቱን ካከናወንን በኋላም እዚያ የተዘጋጀውን ምሳ በልተን በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ተመለስን። ወደ ቤት ስንገባም ልጆቼ እነ ምህረት፣

ሙሉነሽ ሳትቀር ከአዋሳ መጥታ እኔ አስቀድሜ የነገርኳቸው ዶ/ር ሙላቱ፣ አቶ ሽፈራው፣ አቶ ወልደ አምላክ፣ አቶ ደምሴ፣ አቶ ዘለቀ እና አቶ ታምራት ብቻ በተገኙበት መልካም ጊዜ አሳለፍን። ልጆቼ በደንብ ተዘጋጅተው የደገሱትን በጣም ጥሩ እራት ተመግበንም ሥነ ሥርዓቱ አዲስ አበባ በእራት ፕሮግራም ተጠናቀቀ። እነ ዶ/ር ብርሃኑ እና ዶ/ር ሙላቱም ለእነዚያ በእኔ ለተጠሩ ሰዎች ጭምር ጥሩ አድርገው ደግሰው መልስ ጠሩን እና ትልቅ ግብዣ አካሄዱ።

አስጨናቂው የማግባቱ ነገርም አስደሳች ይሆንልኝ ጀመር። እግዚአብሔር ታደለች በተቀበረችበት ቀን እንደሚያለመልመኝና ፍሬ እንደማፈራ የሰጠኝ የተስፋ ቃል በሕይወቴ ይፈጸም ጀመር። ከሁሉ በፊትም እግዚአብሔር ጨልሞ የነበረው ተስፋዬን አለምልሞት አዲስ ባገባኋት ሚስቴ በጣም ደስ እሰኝ ጀመር። ከበቡሽ የሚለውን ስሟን ቀይሬም ሰላም እያልኩ እጠራት ጀመር።

ሁልጊዜም አብረን ጊዜ ስናሳልፍ እና መጽሐፍ ቅዱስ ስናጠና በኑሮ ውሳኔ ላይ የምታቀርበው ሃሳብ በጣም ደስ የሚያሰኘኝ ሆነ። አንዳንድ ጊዜ አስቀድሞ ብዙነሽን እና ታደለችን የመሰሉ መልካም ሴቶችን ባይሰጠኝ ኖሮ ይህቺን የመሰለች መልካም ሴት የት ቀይታ መጣች ብዬ እቆጭ ነበር እላለሁ።

በእውነት ሰላም እኔን መካሪ፣ በጸሎት ደጋፊ ሳጠፉም የምትገስጽ መልካም የትዳር አጋር ሆነችልኝ።

አንድ ጊዜ ከአዲስ አበባ ወደ ሆሳዕና ለአገልግሎት ከሾፌር ጋር እየሄድኩ እያለ መንገድ ላይ ጎማ ፈነዳና ቆምን። በጊዜው ጎማው እየፈነዳ ያስቸገረን በከመነዳሪው ጥሩ አለመሆን የተነሳ ስለነበር እኔ ከመነዳሪውን የገዛው ሾፌር ላይ ተበሳጭቼ ነበር። በኋላም ባለቤቴ ጋ ደውዬ ስንነጋገር ስለ መንገዳችን ስትጠይቀኝ "ሾፌሩ የተበላሸ ከመነዳሪ ገዝቶ ... " ብዬ በወቀሳ ስሜት መናገር ስጀምር "አፍህን እታብላሽ፤ ሳለሰው አትናገር፤ ዝም ብለህ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገር" ብላ ገሰጸችኝ። እኔም ወዲያው ማስተዋል ችዬ "እግዚአብሔር ይባርክሽ" ብዬአት ስልኩን ዘጋሁ። አንዳንድ ሴቶች ነገር ሲነሳ የሚያቀጣጥል እሳት ይጨምራሉ። ይህቺ ግን እኔን ገስጻ እሳት ታጠፋለች። ይህንን እና ሌሎችንም ብዙ መልካም ነገሮች በማድረግም እግዚአብሔር የሰጠኝ ትክክለኛ ረዳት ሆናኛለች።

በአገልግሎቴም እግዚአብሔር ረድቶኝ ከዓመታት በፊት ሰድሜ እና ጤናዬን አስቤ ከዋና ጽሕፈት ቤት የለቀቅሁት እና በጊዜው እየደከመኝ ቁጭ ብዬ ሁሉ ማስተማር ጀምሬ የነበርኩት ሰው በቀን አራት ጊዜ ያለ ምንም ድካም ቆሜ የማስተምር ብርቱ ሆንኩ። እንደ ካሌብ ከ80 ዓመት በላይ ሆኜ ጉልበቴ ታድሶ እንደገና በመላ አገሪቱ እየዞርኩ የማስተምር አገልጋይ መሆን በመቻሌ ብዙ ፍሬ እና ድልም አገኘሁ።

በጣም በሳል የሆነች ልጅ ስላገባሁም በቤቴም ሰው የሰጋው ችግር ፈጽሞ አልተፈጠረም። ሰላም ከልጆቼ ሁሉ ጋር በፍቅር እና በደንብ ተግባብታ መኖር ችላለች። ልጆቼ እቤት ከመጡ በደንብ ታስተናግዳለች። በኔ ግቢ የሚኖረው ልጄ ኃብተ ወልድንም በፍቅር ቀርባ በደንብ እንደ እናት ሆና ትንከባከበዋለች።

እኔም እግዚአብሔር ለኔ እርሷን እንደሰጠኝና በረከት እንደሆነችልኝ "እኔስ ምን ላድርግላት?" ብዬ ለጠየቅኩት ጥያቄ "አስተምራት" ብሎ በተናገረኝ መሠረት ሰላምን ማስተማር ጀመርኩ። እኔ ባስጀመርኩት የጌጃ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተቋምም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አስተምሬአት በዲግሪ ተመረቀች። በጊዜው ለትምህርት ያስፈልጋል የምትለውን ሁሉ እየገዛሁላት ሳትጉላላ በደንብ ተምራለች።

አስተዋይ ሴት ስለሆነችም ከገጠር እንደመጣ ሰው ሳትሆን የአዲስ አበባን ኑሮ ቶሎ ለምዳ ቤታችንን ቀጥ አድርጋ በማስተዳደር የምንበላውን እና የሚያስፈልገንን ሁሉ ራሷ ማዘጋጀት ጀምራለች። እኔንም የቤት ውስጥ ነገሮችን ከመቆጣጠር አሳረፈችኝ። ስለዚህ እንደገና ትኩረቴ ለተጠራሁለት የወንጌል አገልግሎት ብቻ ሆነ። ብዙዎች ቀደም ሲል ሃሳቤን የተቃወሙም እግዚአብሔር እንዳስመለሰኝ ሲያዩ የተፈጸመው የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ ተረዱ። ይኸው ከአምስት ዓመታት በላይም መልካም የትዳር ጊዜያትን አሳለፍን።

----------------------------//----------------------------

# ምዕራፍ ፵፬

# በልጅ መፈተን

## አባትነት

*ጊዜው 1947 ዓ.ም ነበር። ወጣቱ ወንጌላዊ ኬዳም በወንጌላዊነት እያገለገለ ካለበት የጌዴኦ ምድር ለእረፍት ወደ የትውልድ መንደሩ ሻሾን ተመልሷል። በዚሁ ጊዜ የኬዳም ባለቤት የነበረችው ብዙነሽ አርግዛ ዘጠኝ ወር ስለሞላት በከምባታ ምድር ወዳለው እህቷ ቤት ተወስዳ መውለጃዋ እየተጠበቀ ነበር። ወጣቱ ኬዳም ሻሾን በነበረበት ጊዜም ብዙነሽ ጤነኛ ወንድ ልጅ በሰላም ተገላገለች የሚል ዜና ወጣቱ ወንጌላዊ ይህንን አስደሳች ዜና ሲሰማም የሚያደርገው ግራ ገባው። በጣም ከመደሰቱ የተነሳም በበቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሲያስተምሩት እና ሲመክሩት ወደ ነበሩት ሚ/ር ዶናልድ ለተሰኙ ሚስዮናዊ የሰማውን የምስራች ሊያጋራ ገሰገሰ።*

*ኬዳም ሚ/ር ዶናልድ ያሉበት ደርሶም የመጣበትን ምክንያት ሲነግራቸው ሚስዮናዊው እጅግ ተደሰቱ። በወቅቱ ቀጭን የነበረውን ወጣት ወንጌላዊ በስፖርት በፈረጠመ ክንዳቸው አቅፈው በማንጠልጠል "ብራቮ! ብራቮ!" እያሉ ደስታቸውን ገለጹ። ከዚያም በደስታ የወንጌላዊውን ትከሻ እየቸበቸቡ "ኦ ከአሁን በኋላ አንተ ትልቅ ሰው ነህ።" አሉ። ኬዳምም "ምንድን ነው ትልቅ የሚያስብለኝ?" ብሎ ጠየቀ። ሚስዮናዊውም "በመጀመሪያ አንተ ራስህ ክርስቲያን አገልጋይ ሆነህ ክርስቲያን ሚስት በማግባትህ ነው። ብዙ ወጣቶች ተፈትነው የሚወድቁት ሚስት በማግቢያ ጊዜአቸው ነው። አንተ ግን ያንን ፈተና አልፈህ ክርስቲያን ሚስት በቤተ ክርስቲያን ስነ ሥርዓት አገባህ። ሁለተኛው ደግሞ በዚህ መልኩ ካገባሃት ሚስት ልጅ ማግኘትህ ትልቅ ያሰኙሃል።" አሉት።*

*ኬዳም በሃሳቡ ቢስማማም በአዕምሮው የመጣውን አንድ ጥያቄ ማከሉ ግን አልቀረም። "ልጅ ባይወለድ ኖሮ ምን ይከናል ምን ችግር ይፈጥራል?" ሲልም ጠየቀ። ሚ/ር ዶናልድም በቀላሉ "አዬ ምንም አይከንም ብለህ አታስብ፤ ብዙ ነገር ይከናል" ብለው መለሱ። ወንጌላዊውም በሕይወት ዘመኑ ብዙ ልጅ በማጣት የሚቸገሩ እና የሚፈተኑ ሲያይ የሚ/ር ዶናልድ ምክር ትክክል እንደነበር ይገባው ጀመር።*

-------------------------//-------------------------

## መፈተን

ሚ/ር ዶናልድ ከመከሩኝም በኋላ እግዚአብሔር በልጆች በባረከኝ ቁጥር ሁል ጊዜ ደስ እሰኛለሁ። ልጆች የሰው ልጅ በሕይወቱ ደስ እንዲሰኝ ከእግዚአብሔር የሚሰጡት ውድ ስጦታዎች ናቸው። እኔንም እግዚአብሔር በ8 ልጆች ባርኮኛል። በእናቷ ሕመም የተነሳ እናቴ ጋ ሄዳ የቆየችው እና እያደገች ስትሄድም አያቷን መርጣ ከእኔ ጋር ለመኖር ፈቃደኛ ካልሆነችው ከድንቅነሽ በስተቀር ሰባቱም ልጆቼ እኔ በሄድኩበት ሁሉ አብረውኝ እየዞሩ ከኔ ሳይለዩ በቤቴ አድገዋል።

እግዚአብሔር ጠንካራ ልብ ስለሰጠኝ አጠገቤ ሆኖ እያበረታኝ አሳለፈኝ እንጂ በልጆቼ በኩልም በርካታ አስጨናቂ ፈተናዎች መከሰታቸው አልቀረም። ዳዊት እና ሣራ በአደጋ እና በሕመም ሳቢያ በሞት ተለዩን። ኃብተወልድ በደርግ ዘመን ወደ ጦር ሜዳ ሊወሰድ ተቃርቦ እግዚአብሔር አስመልጦልናል። በዚህ በኋለኛው የዕድሜ ዘመኔም አንድ የልጅ ልጄ በሕጻንነቷ በአደጋ ሞታብን ቀብረናል። በዚሁ ሁሉ ውስጥም እግዚአብሔር አብሮኝ ይሆን ስለነበረ አስጨናቂውን ሁኔታ በድል እየተሻገርኩ ለእግዚአብሔር ክብርን መስጠት ችያለሁ።

ከ1974 ዓ.ም ጀምሮም የመጀመሪያ ልጄ (ድንቅነሽ) ወርቅነህ የሚባል የልጅ ልጄን ከወለደችበት ጊዜ አንስቶ የብዙ የልጅ ልጆች አያት ሆኛለሁ። የልጅ ልጄ ወርቅነህም የራሱን ልጅ ወልዶ ቅድመ አያት አድርጎኛል። በእርግጥ እኔ በሥጋ ከወለድኳቸው ልጆች ያላነሰ እግዚአብሔር በየዘመናቱ የሰጠኝን ብዙ ሺህ ልጆች እያሰብኩ የምደሰት ብሆንም የመረጠኝ እግዚአብሔር የራሴን ትውልድ በማብዛትም በብዙ ባርኮኛል።

ልጆች በማሳደግም እግዚአብሔር የሰጠኝን ኃላፊነት ለመወጣት ምንም እኔ በብዙ የአገልግሎት ሩጫ ተጠምጄ የምኖር ብሆንም አደራዬን ለመወጣት ብዙ ጥሬአለሁ። ልጆቼን በሙሉ የሚያስፈልጋቸውን እያሟላሁ አሳድጌአለሁ። ገጠር ያደገችው ልጄ ድንቅነሽን ሳይቀር እስከ ዛሬ ድረስ ከእርሷም አልፌ የእርሷ ልጅ ለሆነው የልጅ ልጄን ድጋፍ እያደረግሁላቸው ኑሮአቸውን ለማቃናት እጥራለሁ። ከሁሉ በላይም እግዚአብሔር በእኔ ውስጥ የሠራውን እና ለሌሎች እንዳካፍል ያስቀመጠውን ድንቅ ሕይወት እነርሱም እንዲኖሩት እጥራለሁ፤ እጸልይላቸውማለሁ።

ልጆቼ ሕጻናት ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮም በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በቤት የእግዚአብሔርን ቃል ትምህርት እንዲያገኙ ያደረግን ሲሆን እስካሁን ያልተቋረጠና ቤት ውስጥ ባሉ ሰዎች የሚካሄድ የምሽት የቤተሰብ ጸሎት እና የቃል ጥናት ጊዜ አለን። በተለይ ልጆቼ ትንንሽ በነበሩበት ጊዜ እና አድገው በየራሳቸው ነገር እስኪያዙ ድረስ በየምሽቱ አንድ ሰዓት ተሰብስበን እንጸልይ እና የእግዚአብሔርን ቃል እናጠና ነበር።

በየምሽቱም የምንጫወትበት እና የምንማማርበት ጊዜ ነበረን። ልጆቼ እያደጉ ሄደው የየራሳቸውን ሥራ ሲይዙ ግን ያ ሊቀጥል አልቻለም። የምሽት አምልኮአችንና ከልጆች ጋር የነበረው ምክክርም ተስተጓጎለ። ይህ ሁኔታም ከቆይታ በኋላ በልጆች ካየሁት ፈተና ሁሉ የከበደኝን ፈተና በቤታችን አስከተለ።

ልጄ ኃብተወልድ መልካም ባህርይ ይዞ እና ሥራ መሥራት የሚችል ሆኖ ካደገ በኋላ በድንገት በክፉ ልማድ ተጠምዶ ተገኘ። ገና በወጣትነቱ በቴክኒክ ሥራ ጎበዝ ሆኖ በሥራ ችሎታ የሚደነቅ፣ ለጓደኞቹ እና ለሚቀርቡት ሁሉ መልካም ማድረግ የሚወድና በሰዎችም የሚወደድ ቢሆንም ከመንፈሳዊነት ቀስ በቀስ እየራቀ ሄደ። እኔም እርሱን ለመመለስ ደጋግሜ፣ እመክረው ነበር። ሁኔታው ሲከፋም የሁል ጊዜ መታመኛዬ ወደሆነው ወደ አምላኬም ጸለይኩ። የእግዚአብሔርን ቃልም በደንብ ለማስተማር ሞከርኩ። ነገር ግን ውጤት ሊመጣ አልቻለም። አንዳንድ ጊዜም ተቆጥቼ እየተነሳሁ በመግረፍና በቅጣት እድሜው ያለፈውን ወጣት በመደብደብ ለማቅናት ጣርኩ፣ ነገር ግን ፍጹም እየባሰበት ሄደ።

ይባስ ብሎም አንድ ጊዜ እንደወጣ ለስምንት ወራት ወደ ቤት ሳይመለስ ጠፍቶ ቀረ። እኔም ምንም የልጅ መጉደል ቢያሳዝነኝም ለራሴ ግን "እኛ ወልደናል፣ የሚያስፈልገውን ሁሉ እያደረግን እያስተማርን አሳድገናል፣ ቃሉን አስተምረናል፣ ሥራ አስይዘናል። ስለዚህ ከአሁን በኋላ እኔ በእርሱ ሕይወት ተጠያቂ አይደለሁም" ብዬ እርሱን ከውስጤ ለማውጣት እና ራሴን ነጻ ለማድረግ ፈለግሁ። ነገር ግን ልጁን ከውስጤ ለማውጣት እና ለመርሳት በሞከርኩ ቁጥር መንፈስ ቅዱስ መልሶ ወደ እኔ ያመጣዋል። ልረሳው ስሞክር ጭራሽ ወደ እኔ ሃሳብ ከበፊቱ ይልቅ ቀረብ ብሎ ይመጣል። ስለሆነም እግዚአብሔር ስለ እርሱ ምላሽ እንዲሰጠኝ እጸልይ ጀመር።

አንድ ረቡዕ ቀንም ልክ ከቀኑ ሰባት ሰዓት አካባቢ ከቤት ወጥቼ ወደ አንድ ጉዳይ ልሄድ ተነሳሁ። ነገር ግን ስላልቻልኩኝ ወደ መኝታ ቤቴ ተመልሼ በእርሱ ጉዳይ ለመጸለይ ተንበረከክሁ። እግዚአብሔርንም "ምን ላድርግ?" አልኩት። እርሱም መልሶ "ውደደው!" አለኝ። በውስጤም ስለ እርሱ ልዩ የሆነ ፍቅር አፈሰሰብኝ።

ከጸሎት እንደተነሳሁም እርሱ በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት የውሃ ልማት ሥራ ሲሠራ ስለነበር እና ብዙ ሰዎች ስለሚያውቁት በቀጥታ ወደ ጽሕፈት ቤቱ ሄጄ ለአንድ ለምቀርበው ሾፌር "ኃብተወልድን አግኝተኸው ታውቃለህ ወይ?" አልኩት። እርሱም "ከስድስት ቀን በፊት ሻሸመኔ አግኝቼው ነበር።" አለኝ። "ካገኘኸው እባክህን እኔ እንደምፈልገው ንገረው።" ብዬው ተለያየን። ከጥቂት ጊዜ በኋላም አንድ ሐሙስ ቀን አግኝቶት እንደነገረው ነገረኝ። ኃብተ ወልድም በተነገረው በሁለተኛው ቀን ቅዳሜ ዕለት ወደ ቤት መጣ።

የጠፋው ልጄ ወደ ቤት ሲመለስ ጺሙ አድጎ ፊቱን ሞልቶታል፣ ሰውነቱ ሁሉ ተጎሳቁሏል። እኔም እቅፍ አድርጌ ተቀበልኩት እና እየተላቀስን አብረን ጸለይን። ቁጭ

ብለንም ተነጋገርን። እኔም "በቃ ከእንግዲህ ሥራ ፍለጋ አትዙር ቤትህ ግባና ኑር።" አልኩት። ከነበረኝ ገንዘብ ላይ አንስቼም 50 ብር ለሻይ፣ የባንክ ሂሳብ እንዲከፍትም 10 ብር የደብተር እና 100 ብር ተቀማጭ የሚሆን ገንዘብ ሰጠሁት። ሄዶ ገንዘቡን አስገብቶ ደብተሩን ከባንክ ተቀብሎ መጣ።

ከዚያ በኋላ እንደ አዲስ በመዋደድ መኖር ጀመርን። በኋላም በጠና ታምሞ እቤት ስለዋለ ከኔ ጋር እስከ ዛሬ ድረስ በመዋደድና በመከባበር አብረን መኖራችንን ቀጠልን። እርሱ ብዙ ነገር ስለሚያውቅ እኔን በብዙ ነገር ይረዳኛል። እግዚአብሔርም እኔን በዚህ መልኩ አስተማረኝ። ልጅን በማሳደግ ሂደት ውስጥ ጸሎት፣ ፍቅር፣ ትዕግስት፣ እና በምንችለው ሁሉ መርዳት የግድ ሊኖር ይገባል። ይህንን ምክርም በልጆቻቸው ለሚቸገሩ እንዲሁም ወደፊት ልጅ ለሚያሳድጉ የክርስቶስ ተከታይ ወላጆች በሙሉ ለመስጠት እወዳለሁ።

-------------------------//-------------------------

# ምዕራፍ ፴፫

# የመጨረሻው ምዕራፍ

## እንደገና መታደስ

ኪዳም 87 ዓመት ሞላቸው። በወንጌላዊነት አገልግሎትም ከስድስት አስርት ዓመታት በላይ አሳለፉ። ግና አሁንም የክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ፍቅር በውስጣቸው የፈጠረው ግለት አልበረደም። ዛሬም ወንጌልን እንዲሰብኩ፣ መልእክት እንዲያስተላልፉ፣ የተጣሉ እንዲያስታርቁ ከተጠሩ በደስታ ለመሄድ ይነሳሉ። በዚሁ የአገልግሎት ትጋት ላይ እያሉም በ2007 ዓ.ም መጨረሻ ወር አሜሪካ ሄደው እንዲያገለግሉ የአገልግሎት ጥሪ መጣላቸው።

ለሦስተኛ ጊዜ ወደ አሜሪካ ለመጓዝም ይዘገጃጁ ጀመር። በዚሁ ሁኔታ ውስጥ እያሉ ግን ወንጌላዊው ከወትሮው የተለየ የጤና ችግር ገጠማቸውና ሆስፒታል ሄደው ተመርምረው የሃሞት ጠጠር እንዳለባቸው እና በቀዶ ጥገና ሊያስወጡ እንደሚገባ ተነገራቸው። ወንጌላዊው በዚህ ጊዜ ቆመው መሄድ ቢችሉም አሜሪካ ሄደው ለአገልግሎት የጋበዙአቸውን ወገኖች ማስቸገር ስለፈሩም ደውለው ጤናቸው ጥሩ ስላልሆነ መሄድ እንደማይችሉ በመናገራቸው የአሜሪካው ጉዞ ተሰረዘ።

በዚሁ ጊዜ ወንጌላዊው "የእግዚአብሔር ጊዜ ደርሶ ይሆን?" በሚል ሃሳብ ራሳቸውን ያዘገጃጁ ጀመር። ከተጀመረ የቆየውን እግዚአብሔር በእርሳቸው ሕይወት የሠራውን ሥራ የሚተርክ መጽሐፍም ቶሎ እንዲጠናቀቅ አሳሰቡ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም አዲስ አበባ ያለችው የረጲ አጥቢያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ጳጉሜ ወር ላይ ወንጌላዊው እንዲያገለግሏት ጥሪ አቀረበች። ኪዳሞም እንደገና ተነስተው ለማገልገል ሄዱ። ከጤናቸው አንጻር በስጋት የቆሙት ወንጌላዊ በአጥቢያይቱ ጥያቄ መሰረት ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ ስለ መስጠት አስተማሩ። ለአንድ ሰዓት ያህልም በተለመደው ጸጋ ሰበኩ። በዚያው ዕለትም የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በኩሪፍቱ ማዕከል ለምታካሂደው ሥራ የሚሆን 50 ሺህ ብር ከትንሿ አጥቢያ አባላት ተሰበሰበ።

*ከሶናት ቀይታ በኋላ በ2008 ዓ.ም ጅማሬ ላይም ወንጌላዊው በጅማ ከተማ በሚካሄድ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ኮንፈረንስ ላይ እንዲሰብኩ ተጋበዙ። ጤናቸው በጥሩ ሁኔታ ላይ ስለነበረም በአውሮፕላን ወደ ጅማ ከተማ ከበረሩ በኋላ ለአራት ቀናት በተከታታይ እየሰበኩ ድንቅ ጊዜን አሳለፉ።*

*ኃይላቸውን እንደ ንስር ያደሰውን ጌታ እያመሰገኑም እንደገና በ2008 ዓ.ም በአስር የሀል ቦታዎች ለማገልገል እቅድ አወጡ። በተለመደው ኃይል ሊወጡም ተዘጋጁ።*

-------------------------//-------------------------

እግዚአብሔር ታማኝ አምላክ ነው። ራሴን ለእርሱ በመስጠቴ ለአንድም ቀን የማልቆጭበትን የድል ሕይወት ሰጠኝ። ባለቤቴ ታደለች ስትሞት እኔ አበቃ ብዬ ነበር። እርሱ ግን ትለመልማለህ ብሎ እንደገና አለመለመኝ። በ2002 ዓ.ም በአዲስ ትዳር አዲስ ሕይወት አግኝቼ የተጠራሁለትን ወንጌል ማገልገሌን ቀጠልኩ። በ2002፣ በ2003፣ በ2004 ዓ.ም አስደናቂ የአገልግሎት ጊዜያትን አሳልፌያለሁ። በየዓመቱ ብዙ ቦታ እየተጠራሁ አስተማርኩ፣ ሰበክሁ፣ ሥልጠናም ሰጠሁ። ለምሳሌ በ2004 ዓ.ም ብቻ 39 ቦታዎች ነበር ተዘዋውሬ ያገለገልኩት። በየደረስኩብትም ሰዎች በአገልግሎቴ ተባርከው እንደገና እንዳገለግላቸው እግዚአብሔር እንዲፈቅድ እድሜ እንዲጨምርልኝ ስለ እኔ በእምባ ጸልየው ይሸኙኛል።

በ2005 ዓ.ም ዋዜማም እንደ ልማዴ የዓመት እቅድ ለማውጣት እና ለመጸለይ ክረምት ላይ በእግዚአብሔር ፊት ቀርቤ በጸሎት አሳለፍኩ። በሁለተኛው ሳምንት እግዚአብሔር የሰጠኝን የቡራኬ መልዕክት ለቤተ ክርስቲያኒቱ አስተላለፍኩ። በዚህ ዓይነትም በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወርኩ የተለመደውን የትምህርት እና የስብከት አገልግሎት ለጊዜው ከተቀበልኩት የቡራኬ መልዕክት ጋር አድርጌ አቀረብኩ። እንደገናም ብዙ የምባረክበት የድል ዓመት ሆነልኝ። በዚህ ዓመት የቦሌ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን በተከታታይ እንዳስተምር ጋብዞኝ ሄጄ አገለገልኩ። በዚሁ ጊዜም በቤተ ክርስቲያኒቱ ጥያቄና ጌታ አስቀድሞ በሰጠኝ ዓመታዊ መልዕክት መሠረት የቡራኬ አገልግሎት ሰጠሁ።

2006 እና 2007 ዓ.ም በዚህ መልኩ ከጌታ መልዕክት እየተቀበልኩ በተለያዩ ቦታዎች ለአገልግሎት እየተጠራሁ ብዙዎች ከ85 ዓመት በላይ ሲሆኑ እንደሚደክሙት ሳይሆን እኔ እንደ ብርቱ ሰው ሳገለግል ቆየሁ። በአንዳንድ ቦታዎች በቀን አራት ጊዜ ሁሉ አስተምር ነበር። ያለብኝ የስኳር ሕመም እንዳያስቸግረኝ ቅድመ ጥንቃቄ በማድረግ (ስኳሬ ተቃጥሎ እንዳያልቅ ማር ወስጄ እየቆምኩ) አንድም ቀን እንኳን አቃተኝ ብዬ ሳላቆም ብዙ ጊዜ ከአንድ ሰዓት በላይ የእግዚአብሔርን ቃል እየሰበክሁ አገለግያለሁ። በአዲስ አበባ ባሉ ብዙ ቦታዎች ራሴ መኪና እየነዳሁና ወደ ክፍለ አገር ሲሆን ከሾፌር ጋር እየሄድኩ አገለግላለሁ። ታማኝ ሆኖ የገባልኝን ተስፋ እየጠበቀ እግዚአብሔር እንዳሳየኝ የለመለመ የበቀሎ ተክል አለምልሞ በእነዚህ ዓመታት ብዙ ፍሬ ሰጠኝ።

በእነዚሁ ዓመታት እንደ ዕድሜ እኩዮቼ ዕረፍት ወስዶ ለመመለስ ሳይሆን ለማገልገል ብቻ ከኢትዮጵያ ውጪ እንድሄድ ሳይቀር እጠየቅ ነበር። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ደቡብ አፍሪካ ሄጄ እንዳገለግል ተደጋጋሚ ጥሪ የመጣልኝ ቢሆንም አንድ ጊዜ በኤምባሲ አለመፍቀድ፣ ጋባዦቼ የላኩትን ሰነድ አስተካክለው በድጋሚ እንድገባ ሲጠይቁኝ ደግሞ በምሄድበት ጊዜ ስለሚኖረኝ አገልግሎት ሁኔታ ባለመስማማት ቀርቻለሁ።

በድጋሚም በተለይ ከቦቢቻ የአባቶች ማዕከል ግንባታ ጋር በተያያዘ እና በአንድ ቤተ ክርስቲያን ጋባዥነት አንድ ቦታ ብቻ እንድሄድ ተጠይቄ እኔ ከሄድኩ እኔ በሠራሁት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ሥራ የተነሳ የብዙዎች አባት ነኝና በአንድ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ማገልገል አለብኝ የሚል አቋም በመያዜና ጋባዦቼ ደግሞ ባለመስማማታቸው ቀርቻለሁ።

በ2007 ዓ.ም መገባደጃ ላይም ወደ አሜሪካ ሄጄ እስከ 2008 ዓ.ም መጀመሪያ ወር ድረስ እንዳገለግል መጋቢ ግርማ ጋሪ በሚባል የኔ የቀድሞ ተማሪዬ የነበረ አማካኝነት የአገልግሎት ጥሪ መጥቶልኝ ነበር። እኔም በመስማማት ለጉዞ የሚያስፈልገውን ዝግጅት ማድረግ ጀመርኩ። ሆኖም ገና ዓመቱ ሳይገባደድ በዚሁ ሁኔታ ላይ እያለሁ የጤንነቴ ሁኔታ ተቃወሰ። ባደረግሁት ምርመራም የሀሞት ጠጠር እንዳለብኝ እና በቀዶ ጥገና ማስወጣት እንደሚገባኝ ተነገረኝ። እኔም ከነ ሕመሜ ሄጄ የሰዎች ፕሮግራም እንዳላስተጓጉል ለመቅረት ወስኜ ይህንኑ ደውዬ አስታወቅኋቸው።

ከታመምኩ በኋላ ለተወሰኑ ጊዜያት በቤቴ እረፍት ወስጄ ሃኪሞች የሰጡኝን ምክርም ተቀብዬ ተግባራዊ አደረግሁ። እግዚአብሔር ረድቶኝም ጤንነቴ ተሻሻለ። የረጲ አጥቢያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ባደረገችልኝ ግብዣ መሠረት ጳጉሜ 1 ቀን 2007 ዓ.ም እሁድ ቀን ሄጄ አገለገልኩ። ከሕመሜ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለነበረም ጌታ አቅም እንዲሰጠኝ በጣም ጸለይኩ። በብዙ ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ ቆምኩ። አቅቶኝ እንዳላቆም ስጋትም ነበረኝ ጌታም ረዳኝ ለአርባ አምስት ደቂቃ ያህል ሰው ሁሉ ልቡ የተነካበትን መልእክት አቀረብኩ። በዕለቱ ለእግዚአብሔር ቤት ገንዘብን ስለመስጠት አስተምሬ 250 ያህል ሰው ብቻ ከተሰበሰበበት ጉባዔ 50 ሺህ ብር ያህል ገንዘብ ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ ተሰበሰበ። እኔም ኃይሌን ያደሰውን ጌታዬን እያመሰገንኩ ወደ ቤቴ ተመለስኩ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላም በ2008 ዓ.ም መግቢያ ላይ ጅማ በሚካሄድ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ኮንፍረንስ ላይ እንዳገለግል በዋና ጽ/ቤቱ አማካኝነት ተጠየቅሁ። እግዚአብሔር ረድቶኝም ለአራት ቀናት ልዩ ልዩ የአገልግሎት ጊዜ ወደ ጅማ በአውሮፕላን አቀናሁ። በአራቱ ቀናትም ለነበሩ የመላው የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የመንፈሳዊ ዘርፍ አገልጋዮች፣ የምዕራብ ቀጣና ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና አገልጋዮች ከጌታ የተቀበልኩትን መልእክት አስተላለፍኩ።

በመጀመሪያው ቀን ሰውነታችሁን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ መስዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ በሚል፤

በሁለተኛው ቀን ጸሎት እግዚአብሔርን በማወቅ፣ እርሱ ለልጆቹ ያዘጋጀውን ክብር በማወቅ፣ የእግዚአብሔርን ኃይል በማወቅ የሚደረግ ስለመሆኑ፤

በሦስተኛው ቀን ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንደመከረው የማያሳፍር ሠራተኛ ለመሆን ስለመትጋት እና የማያሳፍር ሠራተኛ መሆን እንደሚገባ፤

በአራተኛው ቀን እግዚአብሔር አብ እርሱን ስሙት እንዳለ ኢየሱስን መስማት እንደሚገባ ምንም ሳልቸገር ካስተማርኩ እና ከሰበክሁ በኋላ በብዙ ደስታ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን እና የምዕራብ ቀጣና ቢሮም በነበረኝ የአገልግሎት ቆይታ በሚገባ ተንከባክበው ጥሩ ሆቴል አሳርፈው እንዳልጎዳ ተጠነቀቁልኝ። በስፍራውም የተሰበሰበው ክርስቲያን ሁሉ ከእግዚአብሔር ለመጣው መልዕክት ታዝዞ በእንባ ንስኃ ሲገባ አየሁ።

ወደ አዲስ አበባ ከተመለስኩ በኋላም ጥቂት እንደቆየን ላለፉት 60 ዓመታት ያህል የማውቃቸው በጌኛ ቃለ ሕይወት የአገልግሎት አጋሬና በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት አለቃዬ የነበሩት ዶ/ር ሙላቱ ባፋ በ85 ዓመታቸው ወደ ጌታ ሄዱ። እኔና መሰል ወዳጆቻቸውም በአጋራችን መለየት ብናዝንም እንደሌሎቹ የቀደሙ የወንጌል አርበኞች ሁሉ በዶ/ር ሙላቱ ሞትም ታላቅ የወንጌል ኮንፍራንስ ልናዘጋጅ ተሰናዳን።

ዶ/ር ሙላቱ በቃለ ሕይወት ትልቅ ሥራ የሠሩ በዓለም አቀፍ ደረጃም እውቅና ያተረፉ ትልቅ ሰው ስለነበሩም ለቀብራቸው ብዙ ሕዝብ ተሰበሰበ። በቃለ ሕይወት ዋና ጽ/ቤት ግቢም ታላቅ የሽኝት ስነ ሥርዓት ተካሂዶ ቀኑን ሙሉ ለማለት በሚያስችል ሁኔታ እግዚአብሔር በዶ/ር ሙላቱ ስለሠራው ሥራ ስሙ ተወደሰ። እኔም እንደተለመደው ላለፉት 62 ዓመታት ሳደርግ እንደነበረውም በዶ/ር ሙላቱ ቀብር ላይ ጀግና ጓደኛዬን በማሰብ ጌታ በእርሱ የሠራውንም ስለነገ ምን መሆን እንዳለበትም ለተሰበሰበው ሕዝብ መልዕክት አቀረብኩ። በብዙ ታላላቅ የወንጌል አርበኞች ቀብር ላይ ስሰብክ እንደማደርገው የዶ/ር ሙላቱን የወንጌል ዓርማ አንስተው ወደፊት የሚቀጥሉ ወጣቶችን ጋበዝኩ። የዋና ጽ/ቤቱ ወጣት ሠራተኞችም በዚሁ መንፈስ እንዲቀጥሉ አስነስቼ ቃል አስገባሁ። ይህን የወንጌል ዓርማ የመረከብ ቃል ኪዳን በነ አባባ ጎሴ፣ በነ ወንጌላዊ መስፍን ተስፋዬ እና በሌሎች በርካታ የወንጌል አርበኞች ቀብር ላይ ብዙ ወጣቶችን ቃል ኪዳን ያስገባሁ ሲሆን በዶ/ር ሙላቱም ቀብር ቀን የዶክተሩን ዓርማ ለማንሳት ብዙዎች ቃል ገቡ። እንደ ዶ/ር ሙላት ሁሉ እኔም ነገ ወደ ወደ ጌታ

አልፋለሁ። የወንጌል ዓርማችን ግን በኛ ተተኪዎች ተነስቶ እስከ ጌታ ምጽአት ድረስ አገልግሎቱ ይቀጥላል።

እኔ አሁን 88 ዓመት ሞልቶኛል። አብረውኝ ያሉት የስኳር እና የደም ብዛት ሕመሞች አንድ ቀን ከ65 ዓመት በላይ ስለስሙ ወደ ተናገርኩለት ጌታ ያደርሱኛል ብዬ በደስታ እና በጉጉት እጠብቃለሁ። ጌታ በቃሉ እንደተናገረኝ ልጄ ብሎ ሲቀበለኝና ከእርሱ ጋር ስሆን በእጅጉ ለማየትም እናፍቃለሁ።

አቤት! እግዚአብሔር የሻሾነ ገጠር እረኛ የነበረውን ምስኪን አስነስቶ በዓለም ዙሪያ አዙሮ የራሱ ክብር መገለጫ አደረገው። እግዚአብሔር እንዴት ድንቅ ታማኝ መልካም አምላክ ነው! ክብር ለታላቅ ስሙ ይሁን!!



የሃገር ልብስ አልብሰው ወደ
ቤተክርስቲያን ወሰዱኝ




የሃምሳ ዓመት አገልግሎት መታሰቢያ




የነፓ/ር ሞገስ መስተንግዶ መቼም አይረሳም



ቤተሰቤ



ጻድቅ እና ቤተሰቡ በአሜሪካ





ከአያቷ ጋር በሻሾጎ ያደገችው ልጇ ድንቅነሽ ከልጆቿ ጋር






ሙሉና ቤተሰቧ




ዶ/ር ተከለአብ እና ቤተሰቡ



ዮሴፍ እና ቤተሰቡ




ምህረት እና ቤተሰቧ



ሃብተወልድ



እኔ ሰላም ብዬ የምጠራት ሦስተኛዋ ባለቤቴ ከበቡሽ መኮሮ



በአዲስ አበባ የተገኙት በቅሎና ጎጆ




ሳማሪታንስ ፐርስ የገዛልኝ የወንጌል ፈረሴ (ሚትሱቢሺ)